የዘካህ ሀግጋች

አጭር ማብራሪያ

ኢክያስ አሕመድ

1445 ዓ.ሂ

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

የሁለተኛው እትም መቅድም

ይህ አጭር ጥንቅር በመሰረቱ በ2003 ዓ.ል ለተዘጋጀ የመፅሄት ህትመት ግብአት እንዲሆን በውስን ቀናት የተፃፈ ስለነበረ እጥር ምጥን ያለ ይዘት ነበረው። ከዚያም ያለምንም ለውጥ በወረቀት ህትመትና በኢንተርኔት ሲዘዋወር ቆይቷል።

አሁን ደግሞ ከተወሰኑ ማሻሻያዎች ጋር አንባቢያን ዘንድ እንዲደርስ በማለም ይህን ሁለተኛ እትም ለመላው ህዝበ ሙስሊም አበረክታለሁ።

በዚህኛው እትም ላይ የተካተቱ ጥቂት ለውጦችን በሶስት አበይት ነጥቦች ማቀፍ ይቻላል፦

1/ የቅደም ተከተል ለውጥ ሲሆን ለምሳሌ፦ የገንዘብና የንግድ ሸቀጦችን ዘካህ ማብራሪያ ከእንስሶችና ከአዝርእት ዘካህ ማብራሪያ በፊት እንዲሆን አድርጌያለሁ።[1]

2/ በመጀመሪያው እትም ላይ ያልተጠቀሱ ጥቂት ንዑስ ጭብጦች ታክለዋል።

3/ አንዳንድ ቦታዎች ላይ የገለፃ ማሻሻያዎችና ተጨማሪ ማብራሪያዎች ተካትተዋል።

---

(1) ብዙሃኑ የፊቅህ ሊቃውንት የዘካህ ንብረቶችን አስመልክቶ የተላለፈውን ሐዲሥ መሰረት በማድረግ በቅድሚያ የግመሎችን ዘካህ በማብራራት ይጀምራሉ። ሆኖም በዚህ እትም ላይ የአብዛኛውን አንባቢ ተጨባጭ ሁኔታ በማገናዘብ በቅድሚያ የገንዘብንና የንግድ ዘካህ ህግጋትን አስቀድሜያለሁ።

በተረፈ ጥንቅሩ ለጀማሪዎች መነሻ፣ ለባለሃብቶችም ቀላል መመሪያ እንዲሆን እንጂ በንዑስ ጉዳዮቹ ላይ ማስረጃዎችንና የሊቃውንትን የሀሳብ ልዩነት በዝርዝር ለመዳሰስ የተዘጋጀ አይደለም።

ኢልያስ አሕመድ

ረመዳን 1445



ዘካህ

የስርወ-ቃሉ ጥሬ ፍቺ፡- "መብዛት"ን፣ "ማደግ"ን፣ "መጨመር"ን እንዲሁም "ማወደስ"ንና "(ከእንከን) ማጥራት"ን የሚያመለክት ነው።

የዘካህ ሸሪዓዊ መልእክት ደግሞ፡- *ውሰን መጠን ከደረሱ ውሰን የንብረት ዓይነቶች ተወስዶ ለሚገባቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች የሚሰጥ ግዴታዊ የምፅዋት ወጪ ነው።*

ዘካህ የምፅዋት ዋና ገፅታ በመሆኑ በብዙ ቁርኣናዊና ሐዲሣዊ አገባቡ ሰደቃ (صدقة) በሚለው ቃል ተወስቷል።

የዘካህ ምድራዊ ጥበቦች

የዘካህ ድንጋጌ እንደሌሎቹ መለኮታዊ ህግጋት ሁሉ ከአምልኮ ዘርፍነቱ ባሻገር ድንቅ፣ ብርቅና ፅድቅ ጥበቦችንና ዓላማዎችን ያነገበ ነው። ሰዎች ሊረዷቸው ከሚችሏቸው ግለሰባዊና ማሕበራዊ ጥቅሞቹና የመፍትሄነት ገፅታዎቹ መካከል፡-

- ☑ ለችግረኞች መረጃ መሆኑ፣
- ☑ ለድሆች መቋቋሚያ መሆኑ፣
- ☑ በእምነት ላይ የተመሠረተ የወዳጅነትና የወንድማማችነት ትስስርን ማጥበቁ፣
- ☑ ስብዕናን ከስስትና ከንፉግነት ማፅዳቱ፣
- ☑ ድሆች ለሀብታሞች ያላቸውን ምልከታ ከምቀኝነት ማጥራቱ፣
- ☑ በድህነት ምክንያት የሚፈጸሙ ወንጀሎችን መገደቡ፣
- ☑ ከገንዘብ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጥቅል ኢስላማዊ ጉዳዮችን ለማቀላጠፍ ምክንያት መሆኑና፣
- ☑ የንብረት በረከትን ማስከተሉ የሚጠቀሱ ናቸው።

በኢስላም ያለው ደረጃና ብይን

ዘካህ ኢስላም ከተገነባባቸው አምስቱ መሠረቶች 3ኛው ሲሆን ሸሪዓዊ መስፈርቶቹን ባሟላ ማንኛውም ባለንብረት ላይ ግዴታ መሆኑ ያለምንም ውዝግብ የተረጋገጠ እውነታ ነው። ይህንን የሚያስገነዝቡት ቁርአናዊና ሐዲሣዊ አስተምህሮቶች በርካታ ናቸው፤ ከነዚህም ውስጥ፦

◄ ﴿فَإِن تَابُواْ وَأَقَامُواْ ٱلصَّلَوٰةَ وَءَاتَوُاْ ٱلزَّكَوٰةَ فَإِخۡوَٰنُكُمۡ فِي ٱلدِّينِ﴾[التوبة:١١]

►*«(ተፀፅትው) ከተመለሱ ሰላትንም ካዘወተሩ ዘካህንም ከሰጡ የእምነት ወንድሞቻችሁ ናቸው።»*

◄ عَنْ ابْنِ عُمَرَ – رَضِيَ اللهُ عَنْهُمَا – قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ ﷺ: «بُنِيَ الْإِسْلَامُ عَلَى خَمْسٍ: شَهَادَةِ أَنْ لَا إِلَهَ إِلَّا اللهُ وَأَنَّ مُحَمَّدًا رَسُولُ اللهِ، وَإِقَامِ الصَّلَاةِ، وَإِيتَاءِ الزَّكَاةِ، وَالْحَجِّ، وَصَوْمِ رَمَضَانَ»

► ዓብዱላህ ኢብኑ ዑመር የአላህ መልዕክተኛ ﷺ እንዲህ ብለዋል አሉ፦

«ኢስላም በአምስት ነገሮች ላይ ተገነባ፦ ከአላህ በቀር አምላክ እንደሌለና ሙሐመድም የአላህ መልዕክተኛ መሆናቸውን መመስከር፣ ሰላትን ማቋቋም፣ ዘካን መስጠት፣ ሐጅ ማድረግና ረመዳንን መፆም» (1)

---

(1) አል-ቡኻሪ (8)፣ ሙስሊም (16)

ዘካህን ያለመስጠት ብይን

ዘካን ወጪ የማያደርግ ባለሀብት ከሁለት ምድቦች በአንዱ የሚካተት ነው:-

1ኛው ዓይነት:- የዘካህን ግዴታነት ከማስተባበል ወይም ከኩራትና ከትዕቢት በመነጨ እምቢተኝነት የተነሳ የሚነፍግ ነው፤ ይህ ዓይነቱ ከኢስላም ምንም ድርሻ የሌለው ከሀዲ ስለመሆኑ ጥርጥርም ውዝግብም የለም።

2ኛው ደግሞ:- ግዴታነቱን ሳያስተባብል በስስት ወይም በመዘናጋት የተነሳ የሚነፍግ ሲሆን ለእንዲህ ዓይነቱ የሚገባውን ብይን አስመልክቶ የኢስላም ሊቃውንት ሁለት አመለካከቶች አሏቸው፤

ጥቂቶች ይኸኛው እንደመጀመሪያው ከኢስላም እንደሚወጣ ሲፈርዱ ብዙሃኑ ግን ወንጅሉ ከባድ ቢሆንም ከኢስላም የሚያስወጣው የክህደት እርከን ላይ እንደማያደርሰው ይናገራሉ።

መልዕክተኛው ዘካን በአግባቡ ወጪ የማያደርግ ሰው በፍርዱ ቀን የሚያጋጥመውን ቅጣት ባወሱ ጊዜ:-

◄ «..فيُرى سبيلَه؛ إما إلى الجنة، وإما إلى النار!»

► *«...ከዚያም መንገዱን ይጠቆማል፤ ወይ ወደ ጀነት፤ ወይም ወደ እሳት!»* (1)

ማለታቸው ዘግይቶም ቢሆን ጀነት የመግባት እድል እንዳለው በግልፅ የሚያሳይ በመሆኑ የአብዛኛዎቹን አቋም አመዛኝ ያደርገዋል።

---

(1) ሙስሊም (987)

ዘካህ ግዴታ የሚሆንባቸው ጥቅል መስፈርቶች

ዘካህ ማውጣት ግዴታ የሚሆነው የሚከተሉት አምስት መሥፈርቶች ሲሟሉ ብቻ ነው፡-

1- ሙስሊም መሆን
2- ከባርነት ነፃ መሆን
3- ሙሉ ባለቤትነት
4- ንብረቱ «ኒሷብ» መድረሱ
5- ንብረቱ በባለቤቱ ይዞታ ስር ሆኖ በጨረቃ አቆጣጠር አንድ ዓመት ማስቆጠሩ ፡-

የመስፈርቶቹ ማብራሪያ

1. **ሙስሊም መሆን፡-** ሙስሊም ያልሆነ ሰው ከዘካህ በፊት ሊያሟላቸው የሚገቡ መሠረታዊ ቅድመ ሁኔታዎች ስላሉ እንደ ሙስሊሞች ዘካህ እንዲሰጥ አይጠየቅም። ነገር ግን ሙስሊም ባለመሆኑና ዘካህን ጨምሮ ሌሎች ኢስላማዊ ግዴታዎችን ባለመወጣቱ፣ እንዲሁም በዝርዝር ጥፋቶቹ መንስኤነት የወደያኛው ዓለም ቅጣት እንደሚነባበርበት የሚጠቁሙ ቁርአናዊ ማስረጃዎች አሉ።

2. **ከባርነት ነፃ መሆን፡-** በባርነት ስር ያለ ግለሰብ የንብረት ባለቤት አይሆንምና በእጁ ለዘካህ የደረሰ ንብረት ቢኖር እንኳ ዘካውን የማውጣቱ ሃላፊነት ሎሌውን ሳይሆን አለቃውን የተመለከተ ነው።

3. **ሙሉ ባለቤትነት፡-** አንድ ሰው በይዞታው ስር ለሌለ ንብረት ዘካህ የማውጣት ግዴታ የለበትም፤ በውል ባልተረጋገጠ ባለቤትነት ላይ ያለው ፍርድም ተመሳሳይ ነው። ለምሳሌ፡- በፍርድ ቤት በይዞታ

ክርክር ስር ያለ ንብረት ዘካህ አይመለከተውም፤ የጠፋ ወይም የተሰረቀ ንብረትም እንዲሁ።

ውስን ባለቤት በሌለው ንብረት ላይም ዘካህ አይደነገግም። በዚህም መሰረት በ«ወቅፍ» እና በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ይዞታ ስር በሚገኝ ንብረት ላይ ዘካህ አይደነገግም።

ከዚህ (ከ3ኛው) መስፈርት ጋር የተያያዘ አንድ አብይ ርዕስ አለ፡-

- **ዘካህና ዕዳ፡-**

ዕዳ በዘካህ ላይ የሚያሳድረውን ትፅእኖ አስመልክቶ የኢስላም ሊቃውንት የተለያየ አቋም ይዘዋል። ምናልባት ሚዛን የሚደፋው አመለካከት በሚከተለው መልኩ ሊጠቀስ ይችላል፡-

ሀ- ባለ ዕዳውን (ተበዳሪውን) (المدين) በተመለከተ፡-

ዕዳ እያለበት በእጁ ለዘካህ የደረሰ ንብረት ያለው ሰው ዕዳውን የሚከፍልበት ጊዜ ካልደረሰ ከዘካህ ሒሳቡ ላይ ዕዳውን አይቀንስም። ምክንያቱም በእጁ ባለው ውስን (مُعَيَّن) ንብረት ወይም ገንዘብ መጠቀም እስከቻለ ድረስ ባለቤትነቱ የፀና ነውና ዘካውን የማውጣት ሐላፊነት ይኖርበታል። የእዳው ባለቤት (አበዳሪው) ባለ እዳው (ተበዳሪው) ዘንድ ያለው እዳ ከጫንቃው ጋር የተያያዘ (في الذِمَّة) እና በአይነት የሚገለፅ ንብረት እንጂ በእጁ ካለው ውስን ንብረት ጋር የግድ የተያያዘ አይደለምና።

ንብረቱ በእጁ እያለ ዕዳውን የሚመልስበት ወቅት ከደረሰ ግን መጠኑን ቀንሶ ሒሳቡን ያሰላና እዳውን ይከፍላል። የተቀረው መጠን ለዘካህ ብቁ ከሆነ (ኒሷብ ከደረሰ) የሚገባውን ወጪ ያደርጋል። ዘካህም እንደ

እዳ ንብረትን የተመለከተ ግዴታ ነውና ሁለቱንም ግዴታዎች ሳይወጡ መቅረት አይቻልም።

ለ- የዕዳው ባለቤትን (አበዳሪውን) (الدائن) በተመለከተ፡-

ሌሎች ዘንድ የዕዳ ንብረት ያለው ግለሰብ በነርሱ ጫንቃ ላይ ያለውን ዕዳ አስመልክቶ ስለሚደነገገው የዘካህ ብይን ለመረዳት በቅድሚያ እዳ ሁለት አይነት እንደሆነ ማወቅ ተገቢ ነው፡-

አንደኛው፡- ከተወሰነ የጊዜ ገደብ በፊት ክፍያው መፈፀሙ ግዴታ እንዳልሆነ በስምምነት የፀደቀ (مُؤَجَّل) ነው።

የእንዲህ አይነቱ ዕዳ መክፈያ ጊዜ ካልደረሰ ባለቤቱ በፈለገው ጊዜ በእጁ የሚያገኘውና የሚጠቀምበት ባለመሆኑ **ዘካህ የማውጣት ግዴታ የሌለበት መሆኑ** አመዛኝ ነው፤ በዚህም ላይ ባለ ዕዳው ዘንድ መጠኑ በውል የሚገኝ ከሆነ ዘካውን የማውጣት ሀላፊነት እንዳለበት ከላይ አሳልፈናል፤ በአንድ ንብረት ላይ ደግሞ ሁለት ዘካህ አይደነገግም።

ሁለተኛው የዕዳ አይነት ደግሞ፡- ለክፍያው የተሰጠው ቀነ ቀጠሮ የደረሰ (حالّ)፤ ወይም ቀድሞውኑ የጊዜ ገደብ ያልሰፈረለት ሲሆን ባለ እዳው **ለመክፈል አቅሙና ፍላጎቱ ያለው** (ملي باذل) ግለሰብ ከሆነ በዕዳው ባለቤት ወይም አበዳሪው ላይ በየአመቱ ዘካህ የማውጣት ግዴታ ይኖርበታል፤ ምክንያቱም ንብረቱን በፈለገው ጊዜ ማግኘት የሚችል ከመሆኑ አኳያ ልክ ሌሎች ዘንድ ባስቀመጠው የአደራ ገንዘብ ላይ ባለ ይዞታነቱ እንደሚረጋገጠው ሁሉ በዚህም ላይ ስለሚረጋገጥ ነው።

ሆኖም ባለ ዕዳው ዕዳውን ለመክፈል አቅም ከሌለው፣ "ዛሬ፣ነገ" የሚል ልግመኛ ከሆነ፣ አሊያም ጭራሽ ዕዳውን ከካደ በባለቤቱ ላይ የዘካህ ግዴታ የለበትም። ከዚያ በኋላ እዳው ገቢ ቢሆንለት እንኳ በአመዛኙ የዑለማዎች አቋም መሰረት አዲስ የዘካ አመት ይቆጥራል

እንጂ ላለፉት አመታት የሚያወጣው ግዴታ የሆነ ወጪ የለም። ሆኖም ጉዳዩ የሊቃውንትን ውዝግብ ያስተናገደ ከመሆኑ አንፃር ከጥርጣሬ ለመውጣት ዘካውን ቢያወጣ የሚያስመሰግነው እንጂ የሚያስወቅሰው አይሆንም።
አላህ ይበልጥ አዋቂ ነው።

4. **ንብረቱ «ኒሷብ» መድረሱ፦** የዘካህ ግዴታ የሚጀምርበት አነስተኛ የንብረት መጠን «ኒሷብ» ይባላል። ከዚህ እርከን ያነሰ ንብረት ላይ ዘካህ ግዴታ አይሆንም። ይህ መጠን እንደንብረቱ አይነት የሚለያይ ሲሆን ዝርዝሩ ወደፊት ተብራርቷል።

5. **ንብረቱ በባለቤቱ ይዞታ ስር ሆኖ በጨረቃ አቆጣጠር [1] አንድ ዓመት ማስቆጠሩ ፦**

አመት ያልሞላው ንብረት የዘካህ ግዴታ እንደማይመለከተው የሚያስረዱ ሐዲሦች የተዘገቡ ቢሆንም በርካታ የሐዲሥ ሊቃውንት ከ«ሰነድ» ምርመራ አንፃር ሁሉም «መውቁፍ»[2] እንደሆኑ ይናገራሉ። ሆኖም ይህ መስፈርት ከጥቂት ዝርዝር የውዝግብ አጀንዳዎች በስተቀር በጥቅሉ በሁሉም ስምምነት የፀደቀ ነው።

አመቱ መቆጠር የሚጀምረው ንብረቱ ኒሷብ ከደረሰበት ጊዜ አንስቶ ሲሆን በመሃል ከኒሷብ መጠን ከጎደለ ግን የዘካው ግዴታ

---

(1) በወራትና በአመታት የተገደቡ ሸሪዓዊ ህግጋት ሁሉ ድንጋጌያቸው የሚያያዘው ከጨረቃ አቆጣጠር ጋር መሆኑን ልብ ማለት ይሻል። አንድ የጨረቃ አመት ወደ 354 ቀናት ያክል ያሉት ሲሆን ይህም በአብዛኛው ከፀሀይ አመት በ 11 ቀናት የሚያንስ ነው። ስለሆነም ዘካህን ለማውጣት በፀሀይ አቆጣጠር ላይ መመርኮዝ ዘካህን ያለአግባብ ማዘየት ከመሆኑ ባሻገር ከ32 አመታት በኋላ የአንድ አመት ሙሉ ግዴታን ከምስኪኖች ለመቀነስ የሚያበቃ ነው።
(2) የዘገባው ሠንሠለት በሰሃቦች ላይ የቆመ - የነርሱ ንግግር።

የማይመለከተው መሆኑ የብዙ ሊቃውንት አመዛኝ አቋም ነው። በድጋሚ ለኒሷብ ከደረሰ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አዲስ የአመት ዙር ይታሰብለታል።

ሆኖም አንድ ሰው ለኒሷብ የደረሰ ንብረት እስካለው ድረስ አመት ሳይሞላ አስቀድሞ ማውጣት ይፈቀድለታል፤ እንዲያውም የሁለት አመት ዘካህ አስቀድሞ ማውጣት እንደሚፈቀድ የሚያሳይ ሐዲሣዊ መረጃ አለ።

ታዲያ ይህ መስፈርት የግድ ተፈፃሚ የማይሆንባቸው ሶስት የንብረት አይነቶች እንዳሉ ዑለማዎች በጥቅሉ ተስማምተዋል፦

<u>አንደኛው</u>፦ ጥሬ ማዕድን፣ አዝርዕትና ብቅሎች - የዘካ ጊዜያቸው ምርቱ የሚጣራበት ጊዜ ነውና።

<u>ሁለተኛው</u>፦ ቅድሚያ ከነበሩ ግመሎች፣ ከብቶች ወይም በጎችና ፍየሎች የተወለዱ አዳዲስ ግልገሎች - እነኚህ አመት ባይሞላቸውም ቀድሞ ቁጥራቸው ኒሷብ ከደረሰው ከብቶች ጋር ተዳብለው የዘካህ ሂሳብ ወስጥ ይካተታሉ።

<u>ሶስተኛው</u>፦ የንግድ ትርፍ፤ መነሻ ካፒታሉ አመት ሲሞላው ለትርፉ አብሮ ዘካህ ሊወጣለት ይገባል።

እነዚህ ሶስት የንብረት ዓይነቶች ዓመት ባይሞላቸውም ሌሎች መስፈርቶች ከተሟሉ የዘካህ ግዴታ ይመለከታቸዋል።

- **<u>ወርሀዊ ገቢና መሰል ጭማሪ የዘካህ ንብረቶች፦</u>**

የአመት ዙር ከማይመለከታቸው ከሶስቱ የንብረት አይነቶች ውጭ ለዘካህ የደረሰ የንብረት መጠን ኖሮት አመት ሳይሞላው ተመሳሳይም ይሁን የተለየ የንብረት ጭማሪ ያገኘ ግለሰብ የሚጠበቅበት ለአዲሱ

ንብረቱ አዲስ የዘካህ ዓመት መጀመር እንደሆነ ብዙሃኑ ልሂቃን ያስረዳሉ።
በይዞታው ያለው ንብረት አንዴ ኒሷብ ከደረሰ በኋላ የሚያገኘው ተመሳሳይ ጭማሪ ለብቻው ኒሷብ መድረሱ መስፈርት አለመሆኑን ልብ ይበሉ።
ለምሳሌ፦ መቶ ሺህ ብር ያገኘ ሰው ከ7 ወራት በኋላ ከትርፍ ውጭ 2 ሺህ ብር ቢያገኝ ለ2 ሺህ ብሩ ዘካህ ማውጣት የሚገደደው ለብቻው አመት ሲሞላው ነው።

በዚህም መሠረት ገቢውን የሚያጠራቅም ደሞዝተኛ ጥርቅሙ የዘካህ ኒሷብ ከደረሰበት ጊዜ አንስቶ አመት መቁጠር ይጀምራል። ከዚያ በኋላ በየወሩ የሚያገኘው ደሞዝ ለየብቻው ኒሷብ ባይሞላ እንኳ አመት ሲሞላው 1/40ኛውን (2.5%) ለዘካህ ወጪ ያደርጋል።

ይህ መንገድ ለእያንዳንዱ ወር አዲስ ሒሳብ በማስላት ከአመት በኋላ በየወሩ ዘካህ ማውጣት ስለሚያስፈልገው አፈፃፀሙ ለብዙዎች አሰቸጋሪ ይሆናል።

➔ ስለሆነም የተሻለውና ገር የሆነው መንገድ ኒሷብ ከሞላበት ጊዜ አንስቶ በአመቱ መጨረሻ በይዞታው ያለውን ገንዘብ ባጠቃላይ በማስላት 1/40ኛውን ማውጣት ነው። በዚህ መልኩ በየአመቱ በይዞታው ለሚኖረው ድምር መጠን ተገቢውን ዘካህ አንድ ጊዜ ያወጣል።

ይህ ሲሆን የተወሰነው የገንዘብ መጠን አመት ሳይሞላው በቅድሚያ ዘካህ ይወጣለታል ማለት ነው፤ ይህም የተፈቀደ ነው።

✸ ከእነዚህ መስፈርቶች ጋር **ለአካለ መጠን መድረስና የአእምሮ ጤናማነት** ያልተጠቀሰበት ምክንያት፦ ህፃን ልጆች ወይም

አእምሮአቸው የታወከ ግለሰቦች ምንም እንኳ ሸሪዓዊ ግዴታዎች በቀጥታ ባይመለከቷቸውም ንብረታቸው ግን «ኒሷብ» እስከደረሰ ድረስ በንብረትነቱ ብቻ ዘካህ ሊወጣለት ስለሚገባ ነው፤ የዘካህ ግዴታነት ከንብረቱ እንጂ ከባለንብረቱ ማንነት ጋር ቀጥተኛ ተያያዥነት የለውምና። ዘካውን የማውጣቱ ሃላፊነት ደግሞ የአስተዳዳሪዎቻቸው ይሆናል። ይህ የብዙሀኑ ሊቃውንት አቋም ሲሆን ይህንንም የሚጠቁሙ ንግግሮች ከተለያዩ ሰሓቦች ተዘግበዋል።

ዘካህ ግዴታ የሚሆንባቸው የንብረቶች አይነቶች

ዘካህ በሁሉም ንብረቶች ላይ ግዴታ አይሆንም። በዚህ ረገድ ያሉ ሸሪዓዊ ህግጋትን ስናስተውል ድንጋጌው በጥቅሉ ለመልማትና ለማደግ አቅም ካላቸው የሀብት ይዞታዎች ጋር እንጂ ለተለያዩ ግልጋሎቶች ከሚውሉ መጠቃቀሚያ ንብረቶች ጋር የተዛመደ አለመሆኑን እንገነዘባለን።

◄ عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ: أَنَّ رَسُولَ اللَّهِ –صلى الله عليه وسلم– قَالَ: «لَيْسَ عَلَى المُسْلِمِ فِي عَبْدِهِ وَلاَ فَرَسِهِ صَدَقَةٌ».

► አቡ-ሁረይራህ እንዳስተላለፉት የአላህ *መልዕክተኛ፦ «ሙስሊም በባሪያውና በፈረሱ ላይ ዘካህ የለበትም።»* አሉ።[1]

- **<u>የሐራም ንብረት ዘካህ፦</u>**

በተከለከለ መንገድ በይዞታ የገባ የሐራም ንብረት የዘካ ግዴታ አይመለከተውም፤ እንደ ዘካህ ተቀባይነትም አይኖረውም! ምክንያቱም እያወቀ በሐራም መንገድ ንብረትን የሰበሰበ ግለሰብ ይህንን ሙሉ በሙሉ ከይዞታው ማስወጣት ይጠበቅበታልና። ለምሳሌ፦ ከሰዎች በስርቆትና በማታለል የተወሰደ ንብረት ለባለቤቶቹ ሊመለስ ይገባል። በወለድና እርም የሆኑ ሽቀጦችን በመሸጥ የተገኘ ገቢም ለበጎ አላማ እንዲውል ወጪ ካልተደረገ ንሰሃው የተሟላ አይሆንም።

---

(1) አል-ቡኻሪ (1463)፣ (1464)፤ ሙስሊም (982)

ዘካህ ግዴታ የሚሆነው በጥቅሉ በአራት የንብረት አይነቶች ላይ ነው፤ እነሱም፡-

❶- የዋጋ ተመን የሆኑ ንብረቶች፤ ማለትም ወርቅና ብር (silver) እንዲሁም የዘመናችን የገንዘብ ኖቶች፤

❷- ለሽያጭ የቀረበ የማንኛውም ሸቀጥና ዕቃ ተመን፤

❸- የሚራቡ ግመሎች፣(የቀንድ) ከብቶች፣ በጎችና ፍየሎች፤

❹- ከምድር የሚወጡ ተፈጥሯዊ ሀብቶች፤ ማለትም አዝርዕትና ሰብሎች፤ እንዲሁም በቁፋሮ የሚወጡ ጥሬ ማዕድናት ናቸው።

❀❀❀

የዘካህ ንብረቶች ዝርዝር ህግጋት

1- እንደ ወርቅና ብር ያሉ የዋጋ ተመኖች ዘካህ

የወርቅና የብር ማዕድኖች በቀድሞው ዘመን ዋነኛ መገበያያና የተመን መለኪያ ሆነው ቆይተዋል። ስለሆነም ለዘካህ የደረሰ የወርቅ ወይም የብር (ሲልቨር) መጠን ኖሮት በጨረቃ አቆጣጠር አመት ያሳለፈ ሙስሊም የተወሰነውን ያህል ወጪ ማድረግ እንደሚገባው በሸሪዓችን ፀድቋል።

◄ عن أبي هُرَيْرَةَ، قال: قَالَ رَسُولُ اللهِ –صلى الله عليه وسلم–: « مَا مِنْ صَاحِبِ ذَهَبٍ وَلاَ فِضَّةٍ لاَ يُؤَدِّى مِنْهَا حَقَّهَا إِلاَّ إِذَا كَانَ يَوْمُ الْقِيَامَةِ صُفِّحَتْ لَهُ صَفَائِحُ مِنْ نَارٍ؛ فَأُحْمِىَ عَلَيْهَا فِى نَارِ جَهَنَّمَ؛ فَيُكْوَى بِهَا جَنْبُهُ وَجَبِينُهُ وَظَهْرُهُ، كُلَّمَا بَرَدَتْ أُعِيدَتْ لَهُ فِى يَوْمٍ كَانَ مِقْدَارُهُ خَمْسِينَ أَلْفَ سَنَةٍ... » الحديث.

► ***ከአቡ ሁረይራህ እንደተዘገበው የአላህ መልዕተኛ እንዲህ ብለዋል፦***

«የወርቅና የብር (silver) ባለቤት ሆኖ ግዴታውን የማይወጣ ሁሉ በፍርዱ ቀን (ንብረቱ) እንደ ዝርግ ሳህኖች ተዘርግቶ በጀሐነም እሳት ይግልና ጎኑ፣ ግንባሩና ጀርባው ይተኮሳል፤ (ከዚያም) በቀዘቀዘ ቁጥር (በግለት) ይመለሳል፤ ይህም ልኬቱ ሃምሳ ሺህ አመት በሆነ ቀን ነው...» (1)

ወርቅ ወይም ብር ለሽያጭ፣ ንብረትን ለማጠራቀም ወይም ለተከለከለ ይዞታ ከዋለ ለጌጥነት እንዲያገለግል ተቀርፆ የተሠራ ሆነም አልሆነ

---

(1) ሙስሊም (987)

የዘካህ ህግ እንደሚመለከተው ሁሉም ሊቃውንት ይስማማሉ። የተከለከለ ይዞታ ሲባል ማዕድኑ በመሰረቱ የሐላል ንብረት ቢሆንም በሸሪዓ በተከለከለ መልኩ ግልጋሎት ላይ መዋሉ ማለት ነው። በዚህም መሰረት ከወርቅ ወይም ከብር የተሰሩ የቤት እቃዎች ወይም ወንዶች የሚያጌጡበት ወርቅ ባለቤት ከሀጢያተኝነቱ ባሻገር የዘካህ ግዴታም ይኖርበታል።

ሆኖም እንደ ሴቶች ወርቅ ያለ በሸሪዓ በተፈቀደ መልኩ ለጌጥነት በሚውለው ላይ ያለውን የዘካህ ብይን አስመልክቶ የኢስላም ሊቃውንት ተወዛግበዋል።

ታዲያ ከላይ እንደተመለከተው ጥቅል ቁርኣናዊና ሐዲሣዊ አስረጆች ወርቅንና ብርን በዓይነት ሳይለዩ የዘካህ ድንጋጌን አስፍረዋል።

አልፎ ተርፎም ጌጥን በተለየ መልኩ የተመለከቱ ሐዲሦች ተዘግበዋል። ከነሱም መካካከል፡-

◄ عَنْ عَمْرِو بْنِ شُعَيْبٍ عَنْ أَبِيهِ عَنْ جَدِّه: أَنَّ امْرَأَةً أَتَتْ رَسُولَ اللَّهِ –صلى الله عليه وسلم– وَمَعَهَا ابْنَةٌ لَهَا، وَفِي يَدِ ابْنَتِهَا مَسَكَتَانِ غَلِيظَتَانِ مِنْ ذَهَبٍ، فَقَالَ لَهَا: « **أَتُعْطِينَ زَكَاةَ هَذَا ؟**». قَالَتْ: لاَ. قَالَ: « **أَيَسُرُّكِ أَنْ يُسَوِّرَكِ اللَّهُ بِهِمَا يَوْمَ الْقِيَامَةِ سِوَارَيْنِ مِنْ نَارٍ؟!** ». قَالَ: فَخَلَعَتْهُمَا، فَأَلْقَتْهُمَا إِلَى النَّبِيِّ – صلى الله عليه وسلم– وَقَالَتْ: هُمَا لِلَّهِ –عَزَّ وَجَلَّ– وَلِرَسُولِهِ.

► ***ዐብዱላህ ኢብኑ ዐምር እንዳስተላለፉት አንዲት ሴት ወደ መልዕተኛው መጣች፤ አብራትም ሴት ልጇ ነበረች፤ በልጇም እጅ ላይ ሁለት ግዙፍ የወርቅ አንባሮች ነበሩ። (መልዕተኛውም) «የዚህን ዘካህ ታወጫለሽ?» አሏት። «አይ!» አለች። «አላህ በፍርዱ ቀን በነርሱ ፈንታ ሁለት የእሳት አንባሮች ቢያለብስሽ ያስደስትሻልን?!»***

አሏት። እርሷም ሁለቱንም አውልቃ ወደ መልዕክተኛው ጣለቻቸውና «ለአላህና ለመልዕተኛው (ሰደቃ) ናቸው» አለች። (1)

እንዲሁም ወርቅና ብር በማንኛውም ቅርፅና ይዘት ላይ ቢኖሩ ከጥንት ጀምሮ የዋጋ ተመንና የሀብት መለኪያ ተደርገው ስለሚቆጠሩ በጥቅሉ ኒሷብ ከደረሱ በየአመቱ ዘካውን ወጪ ማድረጉ ተገቢ ይሆናል።

ሆኖም ጉዳዩ የዑለማዎችን የሀሳብ ልዩነት የሚያስተናግድ /የኢጅቲሃድ አጀንዳ/ እንደመሆኑ ከዚህ በፊት በጌጣጌጥ ላይ የዘካህ ግዴታ እንደሌለ ፈትዋ ሰምቶ ወይም የፊቅህ ምርጫን ተከትሎ ሳያወጣ የቀረ ግለሰብ ላለፈው የሚጠበቅበት ማካካሻ የለም።

➔ ከወርቅና ብር ውጪ ያሉ ጌጣ ጌጦች ግን ዋጋቸው ምንም ያህል ቢወደድ ለሽያጭ የተዘጋጁ እስካልሆኑ ድረስ ዘካህ እንደማይመለከታቸው በብዙሃኑ ዑለማዎች ስምምነት ፀድቋል።

የወርቅና የብር ኒሷብ

- **ወርቅን አስመልክቶ** :- የወርቅ ኒሷብ (ዘካህ ግዴታ የሚሆንበት ዝቅተኛ መጠን) 20 ዲናር ነው።

ይህ ገደብ የሰፈረባቸው ሐዲሦች የሰነድ እንከን ባያጣቸውም በበርካታ መንገዶች የተዘገቡ ከመሆናቸው አንፃር መልዕታቸው ስለሚጠናከር ከሞላ ጎደል በሁሉም ሊቃውንት ስምምነት ብይኑ ፀድቋል ማለት ይቻላል።

- 1 የወርቅ ዲናር 1 ሚሥቃል ያህል ይመዝናል።

---

(1) አህመድ (6667)፣ አቡ ዳዉድ (1565)፣ አን-ነሳኢይ (2491)፣ አት-ቲርሚዚ (637)

- 20 ዲናር (ሚሥቃል) በዘመናችን መለኪያዎች ሲገለፅ እንደሚከተለው ይሆናል፦

1 ዲናር ወርቅ = 4.25 ግራም (በብዙሀኑ አቋም)

20 ዲናር = 20 x 4.25 = 85 ግራም

እናም የወርቅ «ኒሷብ» = 85 ግራም ነው ማለት ነው።

- **የብር ማዕድንን አስመልክቶ፦** የብር (silver) ኒሷብ 200 ዲርሀም ነው።

◄ عن أبي سعيد الخدري، عن النبي –صلى الله عليه وسلم– أنه قال: «..وَلَيْسَ فِيمَا دُونَ خَمْسِ أَوَاقٍ مِنَ الْوَرِقِ صَدَقَةٌ..» الحديث

► አቡ ሰዒድ አል-ኹድሪይ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፦ *«..ከአምስት "አዋቅ" በታች በሆነ ብር (silver) ሰደቃ የለም...»* [1]

- "አዋቅ" የ"ኡውቂይያ" ብዙ ቁጥር ሲሆን አንድ "ኡውቂይያ" አርባ የብር ዲርሀም ያህል ነው።[2]

አምስት "አዋቅ" ደግሞ፦ (5 x 40) = 200 ዲርሀም ይሆናል።

የ200 ዲርሃም የግራም ልኬት እንደሚከተለው ይሰላል፦

- 1 ዲርሃም = 2.975 ግራም (በብዙሀኑ አቋም)
- 200 ዲርሀም = 200 x 2.975 = 595 ግራም

እናም የብር (ሲልቨር) «ኒሳብ» = 595 ግራም ይሆናል ማለት ነው።

---

(1) አል-ቡኻሪ (1405)፣ (1447)፣ (1459)፤ ሙስሊም (979)

(2) አንዳንዶች "ኡውቂያ"ን ወቄት የሚል ፍቺ ይሰጡታል፤ ሆኖም ወቄት ከኡውቂያ በጣም የሚያንስ መጠን እንዳለው ማስተዋል ያሻል።

- **ወጪ የሚሆነው መጠን፡-**

አንድ ሙስሊም በይዞታው ስር ያለ ወርቅ ወይም ብር ከላይ ከተጠቀሰው መጠን ሳይጎድል አንድ የጨረቃ አመት ከሞላ 1/40ኛውን (ወይም 2.5%) ለዘካህ ወጪ ያደርጋል።

አነስ ኢብኑ ማሊክ እንዳስተላለፉት ታላቁ ኸሊፋ አቡ-በክር መልዕክተኛው የደነገጉትን የዘካህ ህግጋት ባብራሩበት ፅሑፍ የሚከተለውን አስፍረዋል፡-

◄ «وَفِي الرِّقَةِ رُبْعُ الْعُشْرِ»

► *«በብር ላይ (ግዴታ የሚሆነው መጠን) የአንድ አሰረኛ ሩብ ነው»*[1]

የአንድ አስረኛ ሩብ ማለት አንድ አርባኛ ነው።

በወርቅ ላይ ያለውም ድንጋጌ ተመሳሳይ መሆኑ በሁሉም ምሁራን ስምምነት ፀድቋል።

ስለዚህ ቢያንስ 85 ግራም ወርቅ ወይም 595 ግራም ብር (ሲልቨር) በይዞታው ያለ ሙስሊም በአመቱ 1/40ኛውን ማለትም (2.5%) ለዘካ ወጪ ማድረግ ይኖርበታል።

ከሌላ ማዕድን ጋር የተቀየጠ ወርቅ ወይም ብር ሌላኛው ቅይጥ አመዛኙን መጠን የያዘ እንደሆነ ወርቁ ወይም ብሩ ለብቻው የሚኖረው የተጣራ ክብደት «ኒሷብ» ካልደረሰ ዘካህ ማውጣት ግዴታ አይሆንም።

---

(1) አል-ቡኻሪ (١٤54)

የቅይጡ መጠን በጣም አነስተኛ ከሆነ ግን የወርቁ/የብሩ የተጣራ ክብደት ለብቻው የኒሷብ መጠን ባይኖረው እንኳ ከሌላኛው ማዕድን ጋር ተደምሮ የኒሷብ መጠን ከደረሰ ከአጠቃላዩ ዘካህ ማውጣት የግድ እንደሆነ የሚናገሩ ሊቃውንት አሉ። ይህንንም ያሉበት ምክንያት በድሮ ጊዜ የዘካህ ግዴታ የተመረኮዘባቸው (የወርቅ) ዲናሮችና (የብር) ዲርሀሞች ሙሉ ለሙሉ የተጣሩ የሚሆኑበት አጋጣሚ እጅግ አናሳ ከመሆኑ ጋር በሁሉም ላይ ዘካህ በመደንገጉ ነው።[1]

ሌሎች ደግሞ እንደመጀመሪያው የተጣራው ንጹህ ወርቅ/ብር ለብቻው እንደሚሰላ ይናገራሉ፤ የዘካህ ህጉ የተያያዘው ከወርቁና ከብሩ ጋር እንጂ ከሌላው ቅይጥ ጋር አይደለምና።

በዚህኛው አባባል መሠረት፡-

- ባለ 24 ካራት ወርቅ ኒሷብ = 85 ግራም

- ባለ 21 ካራት ወርቅ ኒሷብ = 85 x (24 / 21) = 97.14 ግራም

- ባለ 18 ካራት ወርቅ ኒሷብ = 85 x (24 / 18) = 113.3 ግራም

➔ ወርቅ እና ብር የተለያዩ ማዕድኖች በመሆናቸውና እያንዳንዳቸው የተለያየ የኒሷብ መጠን ስለተደነገገላቸው የዘካህ ስሌታቸው በተናጠል እንደሚሰራ የተናገሩ ዑለማዎች አሉ። በዚህ መሰረት እያንዳንዳቸው ለየብቻ ለዘካህ ብቁ እስካልሆኑ ድረስ ግዴታው አይመለከታቸውም ማለት ነው።

---

(1) የተጣራ ንፁህ ወርቅ (24 ካራት) አንፃራዊ በሆነ መልኩ የመለሳለስ ባህሪ ስላለው ለማጠናከር ሲባል እንደ መዳብ ያለ ሌላ ማዕድን እንዲቀላቀልበት ይደረጋል።

ሆኖም ብዙሃኑ የመረጡት አመዛኝ አቋም ወርቅና ብር ለተመሳሳይ ዓላማ የሚውሉ በመሆናቸውና የገበያ ዋጋ ተመንነታቸው የጎላ ከመሆኑ አንፃር ብዙዎች ዘንድ ለዋጋቸው እንጂ ለራሳቸው ምንነት የሚፈለጉ ባለመሆናቸው = በአንድ ላይ ሲዳበሉ የኒሷብ እርከን ላይ የሚደርሱ እንደሆነ የዘካህ ግዴታ የሚመለከታቸው መሆኑ ነው። በዚህ ላይ የንግድ ሸቀጦችን ተመን ከወርቅና ከብር ጋር ደምሮ ማስላት ተገቢ ስለመሆኑ የዑለማዎች ሙሉ ስምምነት መጠቀሱ ይህንን የሚያጠናክር ነው።

ታዲያ የሁለቱን ድምር ኒሷብ መድረሱን ለማወቅ የምናሰላበትን ዘዴ በተመለከተ ከፊሉ ሊቃውንት የእያንዳንዱ ክብደት ከኒሷቡ አንፃር የሚወክለውን የክፉይ መጠን (ፐርሰንት) በመደመር እንደሆነ ሲናገሩ ሌሎች ደግሞ ከዋጋ አንፃር የሁለቱ ድምር የአንደኛው ኒሷብ ላይ መድረሱን በማየት እንደሆነ ይናገራሉ። ሁለቱን አቋሞች በምሳሌ እናብራራ፡-

ከክብደቱ አንፃር፡- አንድ ግለሰብ ግማሽ ኒሷብ ወርቅ (42.5 ግራም) እና ግማሽ ኒሷብ ብር (297.5 ግራም) ቢኖረው የሁለቱ ድምር እንደ ሙሉ ኒሷብ ታስቦ ዘካህ ግዴታ ይሆንበታል። አንዱ በዋጋ ከግማሽ ኒሷብ ያነሰ ቢሆን እንኳ ግዴታው አይቀርለትም ማለት ነው።

ከዋጋ አንፃር ደግሞ፡- አንድ ግለሰብ 100 ዲርሀም ብር (ሲልቨር) እና 5 ዲናር ወርቅ ኖሮት የአምስቱ ዲናር ወርቅ ተመን የ100 ዲርሀም ብር (ሲልቨር) ዋጋ ቢያክል የሁለቱ ጥቅል ዋጋ ከ200 ዲርሀም ዋጋ ጋር ይስተካከላል። ስለሆነም ድምሩ ለዘካህ ግዴታ እንደደረሰ ይታሰባል ማለት ነው። የተሻለውም የስሌት አሰራር እንዲህ የዋጋ መመዘኛ ላይ የተመሰረተ መሆኑ ነው።

➔ በዘካህ ጥቅል መርሆ መሠረት ለወርቅ ዘካህ ወጪ የሚሆነው ወርቅ፣ ለብር ደግሞ ብር ነው። ሆኖም እዚህ ላይ ዋጋውን ተምኖ ላንዱ ሌላውን ማውጣት ወይም በገንዘብ መተካት እንደሚፈቀድ የሚናገሩ ምሁራን በርካታ ናቸው። ይህንን አባባል ከሚያጠናክሩ ምክኒያቶች መካከል አንዱ የወርቅ ኒሷብ 20 ዲናር መሆኑ ነው፤ ታዲያ 20 ዲናር ያለው ሰው የዘካህ ግዴታው ግማሽ ዲናር ሲሆን ዲናርን ለሁለት መግመሱ አስቸጋሪ በመሆኑ ቀላሉ አማራጭ የግማሹን ዲናር ዋጋ በብር ተምኖ ወጪ ማድረግ ይሆናል።

በዚህም መሠረት አንድ ግለሰብ 100 ግራም ወርቅ ቢኖረው የዘካህ ግዴታው 2.5 ግራም ይሆናል፤ ስለሆነም 2.5 ግራም ወርቅ የሚገዛውን ዋጋ በገንዘብ ለዘካህ ወጪ ማድረግ ይፈቀድለታል ማለት ነው።

የገንዘብ ዘካህ

በዘመናችን የዋጋ ተመንነትን ተክቶ የሚገኘው የገንዘብ ኖትን አነሳስና ታሪካዊ ሂደት፣ እንዲሁም በአሁኑ ወቅት ሊሰጠው የሚችለውን ሸሪዓዊ ብይን የተመለከቱ በርካታ ጥናቶች ተደርገዋል።

ባጭሩ የገንዘብ ኖት ለወርቅና ለብር ባለቤትነትና ለእዳ ማረጋገጫ ሰነድ (ሪሲት) ሆኖ ሲዘዋወርበት የነበረው የጥንቱ ተጨባጭ ዛሬ ተቀይሯል።
የዛሬው የኢኮኖሚው ዓለም ነባራዊ ሂደት በግልፅ እንደሚያሳየው የወረቀት ገንዘቡን በሚወክለው የወርቅ ወይም የብር መጠን በባንክ የመቀየር መብት በመሻሩና ያለ ተቀማጭ የወርቅ ሽፋን መታተም በመጀመሩ በኖቶቹ እና በወርቁ ወይም በብሩ መካከል የነበረው ህጋዊ ትስስር ቀርቷል። በዚህም መሰረት የእያንዳንዱ አገር ገንዘብ

(currency) የግዢ አቅም ከአገሩ የኢኮኖሚ ሀይል ጋር የተዛመደ ሆኗል።

ይህም ማለት የገንዘብ ኖት የሰዎች ዋነኛ መገበያያና የዋጋ ተመን መሆኑ በተዘዋዋሪ ከወርቅና ከብር ጋር ቢያመሳስለውም ከሁለቱ ጋር ያለው የእዳ ትስስር ቀርቶ **ራሱን የቻለ የዋጋ ተመን** ሆኗል።

ስለሆነም «ኒሷብ» የደረሰ የገንዘብ መጠን ኖሮት አመት ያሳለፈ ሙስሊም ከገንዘቡ 1/40ኛውን (2.5%) ለዘካህ መክፈሉ የግድ ይሆናል።

ታዲያ ዘካ ግዴታ የሚሆንበት አነስተኛ የገንዘብ መጠን (ኒሷብ) የሚገደብበት መሠረት የወርቅ ኒሷብ ዋጋ ወይስ የብር? የሚለውን ጥያቄ አስመልክቶ ውዝግብ ቢነሳም ብዙሀኑ የዘመናችን ሊቃውንት የመረጡት ሚዛን ደፊ አቋም **በወቅቱ ከሁለቱ የኒሷብ ዋጋዎች አነስተኛ በሆነው ላይ** እንደሚሆን ነው። ከላይ እንዳሳለፍነው የወረቀት ገንዘብ ራሱን የቻለ የዋጋ ተመን መሆኑ ከሁለቱ ኒሳቦች በአንዱ ላይ ብቻ ሳንወሰን ልክ አብዛኛዎቹ ቀደምት ሊቃውንት የንግድ ሸቀጦችን ኒሷብ ስሌት አስመልክቶ እንደፈረዱት **በየትኛውም በኩል አንደኛው የኒሷብ ዋጋ ላይ መድረሱን ብቻ ከግምት እንድናስገባ** ያደርገናል። ይህ ብዙ ሰዎች ዘንድ ወጪ የሚሆንውን የዘካህ መጠን ስለሚያበዛው ለዘካህ ተቀባዮች ይበልጥ ጠቃሚ ይሆናል።

ለምሳሌ፦

➢ ዘካህ በሚወጣበት ወቅት የአንድ ግራም ወርቅ ዋጋ 3,000 የኢት. ብር ቢሆን ይህንን በ85 ስናበዛው የወርቅ ኒሷብን ዋጋ ይሰጠናል፦

➲ 3,000 x 85 = **255,000** ብር ይሆናል፤

➢ የብር (ሲልቨር) ዋጋ ደግሞ በግራም 40 ብር ቢሆን ይህንን በ595 ስናበዛው የኒሷቡን ዋጋ ይሠጠናል፦

➲ 40 x 595 = **23,800** ይሆናል፤

ይህ ውጤት ከወርቁ የኒሷብ ዋጋ ያንሳል። በመሆኑም የገንዘብ ኖት ዘካህ በብር ዋጋ ላይ የተመሠረተ ይሆናል ማለት ነው።

በአሁኑ ጊዜ ያለው ተመን የሚያሳየንም የብር ኒሷብ ዋጋ ከወርቅ ኒሷብ ዋጋ እጅግ እንደሚያንስ ስለሆነ ቢያንስ 595 ግራም ብር የሚገዛ የገንዘብ መጠን ያለው ባለሀብት 1/40ኛውን (2.5%) ወጪ ማድረግ ይጠበቅበታል።[1]

➔ እዚህ ላይ ሁለት ቁም ነገሮችን ማስተዋል ያስፈልጋል፦

አንደኛው፦ የወርቅ እና የብር ዋጋ ቋሚ ባለመሆኑ በየአመቱ የዘካው ግዴታ በደረሰበት ጊዜ በሚኖረው እለታዊ ዋጋ ላይ መመርኮዝ ተገቢ ነው። አንድ ጊዜ ተሰልቶ የተነገረ የገንዘብ ኒሷብ ለሁል ጊዜ አይሰራም።

ሁለተኛው፦ ስሌቱን ስንሰራ የምንመረኮዘው በጌጣጌጥ መሸጫ ዋጋ ላይ ሳይሆን ማዕድኑ ከተጣራ በኋላ ሳይቀረፅ በፊት ባለው ቱባ ይዘቱ /ንፁህ ጠገራ/ ዋጋ ላይ ነው። ይህን ለማወቅ በየአገሩ ያለውን ዋጋ በየቀኑ፣ ብሎም በየሰዓቱ በሚያቀርቡ አስተማማኝ ድረ ገፆች (websites) መታገዝ ይቻላል።

❀❀❀

---

(1) አሁን ባለው የኑሮ ተጨባጭ ይህ መጠን አንድን ግለሰብ የሀብት ባለቤት (غَنِيّ) እነደማያሰኘው በማሰብ ስሌቱ በወርቅ ኒሷብ ላይ መመስረት እንዳለበት የሚናገሩ ዑለማዎች አሉ። ሆኖም የዚህ ተዘዋዋሪ እንድምታ 595 ግራም የማእድን ብር ያለው ሙስሊም ራሱ የማዕድኑ ዋጋ ስለወረደ ዘካህ አይመለከተውም እንደማለት ነው! ይህንን የሚል ማንም የለም። በዚህ ላይ በሸሪዓ የሃብት ባለቤትነት መገለጫ እንደአውዱ ሊለያይ ይችላል፤ በዘካህ ህግ "ሀብታም" የሚሰኘው የኒሷብ ባለቤት ሆኖ አመት ያሳለፈ ነው። በተጨማሪም አመቱን ሙሉ ይህ ንብረት ከኒሷብ ሳይቀንስ በይዞታው ስር መቆየቱ ከኑሮ ግዴታዎች የተረፈ ተቀማጭ እንደሆነ ያሳያል። ከእንዲህ ያለ ገንዘብ በአመት 2.5% ብቻ ወጪ ማድረግ እንደ ጉዳት ሊታሰብ አይገባም።

2- የንግድ ዘካህ

ለሽያጭ የቀረበ ማንኛውም ንብረት ዋጋ ላይ ዘካህ የሚደነገግ ስለመሆኑ በሶሓቦችና በታቢዒዮች ዘመን ተጨባጭ ውዝግብ አይታወቅም። ይህም እንደ ሸቀጣ ሸቀጥ፣ ምግብ፣ የቤት እቃ፣ አልባሳት፣ እንስሳት፣ መሬት፣ ቤት፣ መኪና፣ ማሽን፣ የግንባታ እቃ ያሉ ማንኛውንም የሽያጭ ንብረት የሚያካትት ነው።

የንግድ ዘካህ ግዴታ የሚጀምርበት እርከን (ኒሷብ) ብዙሀኑ ሊቃውንት በመረጡት ሚዛን ደፊ አቋም መሰረት በወቅቱ ከወርቅ ወይም ከብር የኒሷብ ዋጋዎች አነስተኛ የሆነው ነው። ይህም ማለት የንግድ ዘካህ ኒሷብና የገንዘብ ኒሷብ ተመሳሳይ ናቸው።

ወጪ የሚደረገውም 1/40ኛ (2.5%) እንደሆነ ዑለማዎች ዘንድ ያለ ምንም ውዝግብ ፀድቋል።

በዚህ መሰረት የሸቀጦቹ ዋጋ ድምር ለብቻው ወይም ባለቤቱ ዘንድ ካለ ወርቅ፣ ብርና ገንዘብ ዋጋ ጋር ተዳብሎ ከላይ የተጠቀሰውን የጥሬ ገንዘብ «ኒሷብ» የሚያክል ከሆነ ዓመት በሞላው ጊዜ በሚኖረው የገበያ ዋጋ ተተምኖ 1/40ኛው ለዘካህ መውጣት ይኖርበታል።

የንግድ ዘካህን አስመልክቶ ማስተዋል የሚሹ በርካታ ነጥቦች አሉ፡-

1- የንግድ ዘካህ ግዴታ የሚሆነው ለሽያጭ በሚቀርቡ ንብረቶች ዋጋ ላይ ብቻ ነው። በዚህም መሠረት ለንግዱ ተግባር አጋዥ የሆኑ ማሽኖች፣ ማመላለሻ መኪናዎች፣ ታክሲዎች፣ ለኪራይ የተዘጋጁ ንብረቶችና የመሳሰሉት ራሳቸው እንዲሸጡ እስካልተወሰነ ድረስ የዘካ ግዴታ አይመለከታቸውም። ሆኖም ከነዚህ የሚገኘው የገንዘብ

ገቢ ለዘካህ ብቁ ሆኖ ዓመት ከሞላው እንደማንኛውም የዘካህ ንብረት ይታያል።

2- አብዛኛዎቹ ሊቃውንት አንድ የሽያጭ ንብረት ላይ ዘካህ የሚደነገገው ሁለት መስፈርቶች ሲሟሉ እንደሆነ ይናገራሉ፡-

- **አንደኛው፡-** ባለቤቱ ንብረቱን ይዞታው ውስጥ ያስገባው ተግባርን ወይም ውልን በሚጠይቅ እንደግዢ ባልለ መንገድ መሆኑ ሲሆን በዚህ መሰረት እንደ ውርስ ውል በማያስፈልገው ሰበብ ካገኘው ግን ለሽያጭ ቢያቀርበው እንኳ ዘካህ እንደማይመለከተው ይፈርዳሉ።
- **ሁለተኛው፡-** ንብረቱን በይዞታው ውስጥ በሚያስገባበት ወቅት ለንግድ እንደሚውል ማቀዱ ነው። በዚህ መሰረት ለሌላ አገልግሎት የገዛውን እቃ ሀሳቡን ቀይሮ ለንግድ ሽያጭ ቢያቀርበው እስኪሸጥ ድረስ ዘካህ አይታሰብበትም ማለት ነው።

ሆኖም <u>የተሻለው የፊቅህ ምርጫ</u> በየትኛውም ሰበብና እቅድ በይዞታው የገባ ንብረት ለሽያጭ ታቅዶ ከተዘጋጀበት ጊዜ አንስቶ የዘካህ ግዴታ የሚመለከተው መሆኑ ነው።

3- ንብረቱን ለሽያጭ ለማቅረብ በሙሉ ልብ ያልወሰነ ባለ ሃብት ቁርጠኛ ውሳኔ ላይ እስኪደርስ የዘካህ ግዴታ አይመለክተውም። ከዘካህ ለመሸሽ እስካላቀደ ድረስ አመት ሳይሞላ የሽያጭ ሀሳቡን የቀየረ ሰውም ዘካህ የለበትም።

4- ለሽያጭ የቀረበው ንብረት ዘካህ ሲሰላ የሚታሰበው ንብረቱ የተገዛበት ዋጋ ሳይሆን ዘካው በደረሰበት ወቅት የሚሸጥበት የገበያ ዋጋ መሆኑን ማስተዋል ያሻል። ይህ ከሞላ ጎደል የዑለማዎች ውዝግብ የሌለበት ጉዳይ ነው።

◄ عَنْ أَبِي عَمْرِو بْنِ حِمَاسٍ، عَنْ أَبِيهِ، قَالَ: مَرَّ بِي عُمَرُ، فَقَالَ: يَا حِمَاسُ، أَدِّ زَكَاةَ مَالِكَ. فَقُلْتُ: مَا لِي مَالٌ إِلَّا جِعَابٌ وَأُدُمٌ. فَقَالَ: قَوِّمْهَا قِيمَةً، ثُمَّ أَدِّ زَكَاتَهَا

► **አቡ ዐምር ኢብኑ ሒማስ አባታቸው (ሒማስ) እንዲህ ማለታቸውን አስተላልፈዋል፦** *ዑመር (ኢብኑ'-ኸጣብ) በእኔ ዘንድ አለፉና "አንተ ሒማስ ሆይ! የንብረትህን ዘካህ ስጥ!" አሉኝ። እኔም "ከቀስት ኮሮጆዎችና ከለፉ ቆዳዎች ውጭ ሌላ ንብረት የለኝም!" አልኩኝ። እርሳቸውም፦ "በዋጋ ተምናቸውና የዘካህ ግዴታቸውን ስጥ!" አሉኝ።*[1]

ከላይ እንዳየነው ለንግድ ትርፍ አዲስ የዘካህ አመት ሳይታሰብ ከካፒታሉ መነሻ ጀምሮ የዘካህ ወጪው የሚሰላ በመሆኑ ሸቀጦቹ ሳይሸጡ በፊት የሚኖራቸው የዋጋ ጭማሪም ገና ወደ ገንዘብነት ያልተቀየረ ትርፍ ነውና ጭማሪው የዘካህ ስሌት ውስጥ መካተት እንዳለበት ያሳያል። የዋጋ ቅናሽም ካለ ዘካህ የሚመለከተው ሸቀጦቹ የሚያወጡትን የገበያ ዋጋ ብቻ ይሆናል።

ዋጋ ሲባል ነጋዴው በጅምላ የሚሸጥ ከሆነ በአካባቢው የጅምላ ዋጋ፤ በችርቻሮም ከሆነ በአካባቢው የችርቻሮ ዋጋ መሰረት ተተምኖ ስሌቱ ይሰራል ማለት ነው።

ይህም ማለት ስሌቱ የሚያያዘው የዘካህ አመት ዙር ሞልቶ ግዴታው በሚፀናበት ጊዜ ሸቀጦቹ ከሚኖራቸው የአካባቢ የገበያ ዋጋ ጋር

---

(1) አቡ ዑበይድ (ኪታቡ'ል-አምዋል) (2/80)፣ አሽ-ሻፊዒይ (ኪታቡ'ል-ኡም) (3/119)፣ ኢብኑ አቢ ሸይባህ (አል-ሙሶን-ነፍ) ቁ. (10457)

ነው። ነጋዴው ወደ ፊት ለደንበኞቹ በምን ያህል ተመን እንደሚሸጥ በርግጠኝነት አለማወቁ ብይኑ ላይ የሚያሳድረው ተፅእኖ የለም።

5- የሽያጭ እቃዎች ዋጋ በሚሰላበት ጊዜ ወደ ሸቀጥነት ተቀይረው ለሽያጭ የሚቀርቡ ጥሬ ዕቃዎች በጥሬ ዕቃነታቸው ዋጋቸው ተተምኖ ዘካህ ሊወጣላቸው ይገባል።

6- የንግድ ዘካህ ግዴታ የሚሆነው ለሽያጭ በቀረቡት ንብረቶች <u>ድምር ተመን/ዋጋ</u> ላይ እንጂ በንብረቶቹ ራሳቸው ላይ አይደለም። በዚህም መሠረት፡-

6.1 እንደ ከብቶች ያሉ ሌሎች የዘካህ ንብረቶች ለሽያጭ ከቀረቡ መብላቸው ግጦሽም ይሁን መኖ የሚመለከታቸው <u>የንግድ ዘካህ ብቻ መሆኑን ብዙ ሊቃውንት ይጠቅሳሉ፤</u> ስለሆነም ዋጋቸው ተተምኖ የንግድ «ኒሷብ» ከደረሰ 1/40ኛው ወጪ ይሆናል እንጂ ሌላ ግዴታ አይመለከታቸውም።

6.2 በመሰረቱ ለንግድ ዘካህ ገንዘብን እንጂ ሸቀጦቹን ራሳቸውን ወጪ ማድረግ እንደማይቻል አብዛኛዎቹ ዑለማዎች ፈርደዋል። ከላይ እንዳሳለፍነው የኒሷቡ ልኬት በሸቀጦቹ የገበያ ዋጋ ላይ የተገነባ መሆኑ ይህን የሚያጠናክር ነው። ሆኖም የዘካው ግዴታ በደረሰበት ጊዜ የሚያወጣው ጥሬ ገንዘብ የሌለው ነጋዴ መጠኑን እንደ እዳ መዝግቦ ገንዘብ ባገኘ ጊዜ ይከፍላል።

ሆኖም ሸቀጦቹን ራሳቸውን የሚመርጡ የዘካህ ተቀባዮች ካሉና ነጋዴውም የሚደርስበትን የወጪ ልክ በቁሳቁሱ ልክ መጥኖ ማስላት ከቻለ የዘካውን ግዴታ በሸቀጦች ማውጣት ይፈቀዳል።

7- የሸቀጦቹ ዋጋ ድምር ለብቻው የኒሷብ እርከን ላይ ባይደርስ እንኳ ባለቤቱ ዘንድ ካለ ወርቅ፣ ብርና የወረቀት ገንዘብ ዋጋ ጋር ተዳብሎ ኒሷብ ከሞላበት ጊዜ አንስቶ የንግድ ዘካህ ይታሰባል፤ ምክንያቱም የንግድ ሸቀጦች ነጋዴው ዘንድ ለሚያስገኙት ገንዘብ እንጂ ለራሳቸው ምንነት የሚፈለጉ አለመሆናቸው ሁሉንም ተመሳሳይ ይዘት ያላብሳቸዋልና። በመሆኑም የሸቀጦቹን ዋጋ ከጥሬ ገንዘብ፣ ከወርቅና ከብር ጋር መደመር እንደሚገባ ከሞላ ጎደል የፊቅህ ሊቃውንት ይስማማሉ።

በዚህ መሰረት አንድ ሙስሊም ጥሬ ገንዘብና ሌላ የንግድ ሸቀጥ ኖሮት ሁለቱም እያንዳንዳቸው ኒሷብ ያልደረሱ ሆነው የሁለቱ ድምር ኒሷብ ቢሞላ ከድምሩ ዘካህ ማውጣት ይጠበቅበታል።

8- አንድ ነጋዴ የንግድ ሸቀጦችን የገዛበት የገንዘብ ካፒታል የዘካህ አመትን ማስቆጠር የጀመረ ከነበረ ለሸቀጦቹ አዲስ አመት አይጀምርም፤ ከላይ እንዳሳለፍነው ከገንዘቡ የተለየ ብይን ስለማይሰጣቸው የመጀመሪያው የአመት ዙር አይቋረጥም፤ የተለያዩ የንግድ እቃዎችን በየጊዜው ሲገዛና ሲሸጥም እንደዚሁ። በንግዱ ዓለም ለሽያጭ የቀረቡ ንብረቶች እየተሸጡ በሌላ መተካታቸው የተለመደ ነውና <u>ሸቀጦቹ ራሳቸው አመት ሊሞላቸው የግድ አይልም</u>፤ ዘካው የተያያዘው ከሸቀጦቹ ዋጋ ጋር ነውና።

በመሆኑም አንድ ሰው ለዘካህ የደረሰ ጥሬ ገንዘብ በሸዕባን ወር ቢያገኝና አመት ሳይሞላው በገንዘቡ ለንግድ የሚሆኑ ሸቀጦችን ቢገዛ በዘካው ጊዜ ላይ የሚያስከትለው ለውጥ የለም፤ በሚቀጥለው ሸዕባን የሸቀጦቹን ድምር ተመን አስልቶ ዘካህ ያወጣል።

9- ከንግዱ የሚገኘው ትርፍ ከመነሻው የሽያጭ ካፒታል ጋር ተደምሮ ይሰላል እንጂ ለትርፉ ብቻ አዲስ የዘካህ አመት አይጀመርለትም።

ለምሣሌ፡- አንድ ባለሀብት በአመቱ መጀመሪያ በ100 ሺህ ብር ሸቀጦችን ሸምቶ ንግድ ቢጀምርና የ30ሺህ ብር ትርፍ በማግኘቱ በአመቱ መጨረሻ የሽያጭ ካፒታሉ ወደ 130 ሺህ ቢያድግ ዘካህ የሚያወጣው ከ130 ሺህ ብሩ ላይ ይሆናል። በተቃራኒው የ100 ሺህ ብር የንግድ ሸቀጥ ገዝቶ የ20 ሺህ ብር ኪሳራ ደርሶበት በአመቱ ማብቂያ የሽያጭ ካፒታሉ ወደ 80 ሺህ ብር ዝቅ ቢል ዘካህ የሚያወጣው ከ80 ሺህ ብሩ ብቻ ይሆናል ማለት ነው። ስለሆነም በአመቱ መጨረሻ ያለውን ንብረት መጠን ተምኖ 1/40ውን ማውጣት ብቻ ነው የሚኖርበት።

ታዲያ የትርፉ መጠን ለብቻው ኒሷብ መድረሱ የግድ አለመሆኑን ማስተዋል ያሻል።

10- ትርፋቸውን በሽያጭ የሚያገኙ የንግድ ማህበራትና ድርጅቶች ውስጥ የአክሲዮኖች ድርሻ ያለው ግለሰብ አላማው ከድርጅቱ ስራ የሚገኘውን ትርፍ መካፈል እንደሆነ የዘካህ አወጣጡ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

- የድርጅቱ አስተዳደር የአክሲዮኖቹን ዘካህ የሚያወጣ እንደሆነ ግለሰቡ ዳግም ወጪ አይጠበቅበትም።
- ካልሆነ ግን ሁሉም የድርሻውን ያህል ሊያወጣ ይገባል። በዚህ መሰረት የሽያጭ ዕቃዎቹን የገበያ ተመንና ጥሬ ገንዘብ ደምሮ በማስላት ውጤቱን የርሱ የአክሲዮን ድርሻ ከአጠቃላዩ የአክሲዮኖች ብዛት በሚወክለው ክፋይ በማባዛት የዘካህ ንብረቱ ምን ያህል እንደሆነ ማወቅ ይችላል፤ ከዚያም ይህን ለ40 ስናካፍለው ወጪ መሆን ያለበትን መጠን ይሰጠናል።

ሆኖም አክሲዮኖችን በመግዛትና በመሸጥ ላይ የተሰማራ ነጋዴ በይዞታው ያሉት አክሲዮኖችን እንደ ሸቀጥ በመቁጠር የአክሲዮኖቹን የራሳቸውን የገበያ ዋጋ ተመርኩዞ ከዚህ በፊት በተብራሩት

መስፈርቶች መሰረት ዘካውን ያወጣል፤ ይሽኛው ነጋዴ ድርጅቱ/ማህበሩ ዘካህ ቢያወጣ እንኳ የርሱ ዘካህ አይቀርለትም።



3- የሚራቡ ግመሎች፣ የቀንድ ከብቶች፣ በጎችና ፍየሎች

ከነዚህ እንስሶችና ዝርያዎቻቸው ውጪ ሌላ በቀጥታ ዘካህ የሚመለከተው የእንስሳ ዘር እንደሌለ ብዙሃኑ ሊቃውንት ይስማማሉ።

ከነኚህ ዘካህን መስጠት ግዴታ የሚሆነው በፊት ከተጠቀሱት ጥቅል የዘካህ መስፈርቶች ጋር ሌሎች ቅድመ ሁኔታዎች ሲጨመሩ ነው፤ እነሱም፦

1ኛ፦ አመቱን ሙሉ ወይም የአመቱን አብዛኛውን ክፍል መብላቸው በግጦሽ ስምሪት ላይ የተመሠረተ መሆኑ ነው፤ ስለሆነም ቢያንስ በግማሹ የአመቱ ክፍል በባለንብረቱ ወጪ ወይም ልፋት የሚዘጋጅ መኖ የሚቀለቡ ከሆነ የዘካህ ግዴታ አይመለከታቸውም ማለት ነው። ይህ የብዙሃኑ ሊቃውንት አቋም ነው።

አቡ በክር አስ-ሲድ-ዲቅ መልዕክተኛው የደነገጉትን የዘካህ አወጣጥ በዘረዘሩበት ፅሁፋቸው ስለ በጎችና ፍየሎች ሲያወሱ የሚከተለውን ብለዋል፦

◄ «وَفِي صَدَقَةِ الغَنَمِ فِي سَائِمَتِهَا إِذَا كَانَتْ أَرْبَعِينَ إِلَى عِشْرِينَ وَمِائَةٍ شَاةٌ»

«የበጎችና የፍየሎች ሶደቃ ደግሞ፦ <u>በመሰክ በሚሰማሩት</u> ላይ ከአርባ እስከ መቶ ሃያ ባሉት አንድ በግ ወይም ፍየል ነው።»[1]

2ኛው መስፈርት፦ እንስሶቹ ለርባታ፣ ለወተት ወይም ለማደለብ የተያዙ መሆናቸው ነው፤ እናም በዋነኛነት ለሥራ የታሰቡ ከሆነ ዘካህ

---

(1) አል-ቡኻሪይ (1454)

ማውጣት የግድ አይልም ማለት ነው፤ እንደምሳሌ፦ አንድ ግለሰብ ለሸክም ሥራ የሚያከራያቸው ግመሎች ወይም ለእርሻ የሚያጠምዳቸው በሬዎች ቢኖሩት ቁጥራቸው ቢበዛ እንኳ ከነርሱ ዘካህ ማውጣቱ ግዴታ አይሆንበትም።

ለሽያጭ የተዘጋጁ ከሆነ ደግሞ የዘካ አወጣጡ በንግድ ዘካህ መስፈርትና አፈፃፀም መሰረት ከዋጋቸው አንድ አርባኛው ወጪ ይሆናል እንጂ የእንስሶቹ የዘካህ አወጣጥ አይመለከታቸውም።

ከላይ እንደተገለፀው እንስሶቹ በሸሪዓ የተገደበላቸው ኒሷብ (ዘካህ ግዴታ የሚሆንበት አነስተኛ መጠን) ላይ ካልደረሱ ዘካህ ግዴታ አይሆንም። ይህ መጠን እንደ እንስሳው ዓይነት የሚለያይ ሲሆን ዝርዝሩን ቀጥሎ ባሉት ሰንጠረዦች ማስተዋል ይቻላል።

የግመል ዘካህ አወጣጥ

የርቢ ግመሎቹ ብዛት		ለዘካህ የሚወጣው	
ከ	እስከ	ዓይነት	ብዛት
1	4	-	0
5	9	በግ ወይም ፍየል	1
10	14	በጎች ወይም ፍየሎች	2
15	19	በጎች ወይም ፍየሎች	3
20	24	በጎች ወይም ፍየሎች	4
25	35	አንድ አመት የሞላት ሴት ግመል[1]	1

(1) እዚህ ላይ ባለአንድ አመት ሴት ግመል ሳይኖረው ባለሁለት አመት ወንድ ያለው ያንኑ መስጠት ይችላል።

36	45	ሁለት አመት የሞላት ሴት ግመል	1
46	60	ሶስት አመት የሞላት ሴት ግመል	1
61	75	አራት አመት የሞላት ሴት ግመል	1
76	90	ሁለት አመት የሞላቸው ሴት ግመሎች	2
91	120	ሶስት አመት የሞላቸው ሴት ግመሎች	2

➔ ከ120 በላይ ያለው በእያንዳንዱ 40 ግመል ሂሳብ ሁለት አመት የሞላት ሴት ግመል፤ በእያንዳንዱ 50 ግመል ሂሳብ ደግሞ ሶስት አመት የሞላት ሴት ግመል ይከፍላል።

ለምሳሌ፡-

- 130 ግመሎች ያሉት ሰው፡-

130 = 40 ⇩ + 40 ⇩ + 50 ⇩

= 1 የሁለት አመት ሴት ግመል + 1 የሁለት አመት ሴት ግመል + 1 የሦስት አመት ሴት ግመል

= 2 ባለ ሁለት አመት እና 1 ባለ ሶስት አመት ሴት ግመሎች - ይህ እስከ 139 ድረስ አይቀየርም!

- 140 ግመሎች ያለው ሰው፡-

140	=	50	+	50	+	40		
		⇩		⇩		⇩		
	=	1 የሶስት አመት ሴት ግመል	+	1 የሶስት አመት ሴት ግመል	+	1 የሁለት አመት ሴት ግመል		

= 2 ባለ ሶስት አመት እና 1 ባለ ሁለት አመት ሴት ግመሎች - ይህም እስከ 149 ድረስ አይቀየርም!

- 200 ግመሎች ያሉት፡-

200 = 50 x 4 = አራት ባለ ሶስት ዓመት ሴት ግመሎች

ወይም = 40 x 5 = አምስት ባለ ሁለት ዓመት ሴት ግመሎች

ስለዚህ ከሁለቱ መንገዶች በመረጠው ዘካህ ያወጣል ማለት ነው።

➔ ከተገደቡት የዕድሜ ደረጃዎች ያነሰ ወይም የበለጠ ብቻ ያለው ባለ ግመል በእያንዳንዱ የአመት ልዩነት ሁለት በጎች ወይም ፍየሎችን አሊያም 20 ዲርሃም ይከፍላል ወይም ይቀበላል።[1]

---

(1) 20 ዲርሃም ወደ 59.5 ግራም የሚመዝን ብር (silver) ነው።

የቀንድ ከብት (የላምና የበሬ) ዘካህ አወጣጥ

በእያንዳንዱ 30 ከብት ሂሳብ አንድ አመት የሞላው/ት አንድ ወንድ

ወይም ሴት ጥጃ ፣ በእያንዳንዱ አርባ ሂሳብ ደግሞ ሁለት አመት የሞላት ሴት ከብት ያወጣል።

የርቢ ከብቶቹ ብዛት		ለዘካህ የሚወጣው	
ከ	እስከ	ዓይነት	ብዛት
1	29	_	0
30	39	አመት የሞላው/ት ጥጃ	1
40	59	ሁለት አመት የሞላት ጊደር	1
60	69	አመት የሞላቸው ጥጆች	2
70	79	አንድ ባለ አንድ አመት ጥጃና አንድ ባለ ሁለት አመት ጊደር	2

እንዲህ እያለ ይቀጥላል፤

ለምሳሌ፡-

- 80 ከብቶች ያለው ሰው፡-

80 = 40 + 40

⇩ ⇩

= 1 ባለ ሁለት አመት ጊደር + 1 ባለ ሁለት አመት ጊደር

= 2 ባለ ሁለት አመት ጊደሮች

- ይህ እስከ 89 አይቀየርም!

- 90 ያለው ሰው:-

  90 = 3 X 30 = 3 ባለ አንድ አመት ጥጆች

  - እስከ 99 አይቀየርም!

- መቶ ያለው ሰው:-

  100 = 40 + 30 + 30

  = 1 ባለ ሁለት አመት ጊደር እና 2 ባለ አንድ አመት ጥጆች

የበግና የፍየል ዘካህ አወጣጥ

የርቢ በጎቹ/ፍየሎቹ ብዛት		ለዘካህ የሚሰጠው	
ከ	እስከ	ዓይነት	ብዛት
1	39	-	0
40	120	በግ ወይም ፍየል	1
121	200	በጎች ወይም ፍየሎች	2
201	399	በጎች ወይም ፍየሎች	3

ከዚህ በኋላ ላለው ቁጥር በ 100 በጎች/ፍየሎች ሂሳብ አንድ በግ/ፍየል ይወጣል። ለምሳሌ፡-

- 400 በግ ያለው ሰው 4 በጎች/ፍየሎች ያወጣል።

  - ይህ እስከ 499 አይቀየርም!

- 500 ያለው አምስት ያወጣል። ይህም እስከ 599 አይቀየርም።
- 600 ያለው 6 ያወጣል። እንዲህ እያለ ይቀጥላል።

➔ ለዘካህ ወጪ የሚደረጉት በጎች ቢያንስ 6 ወር ፤ ፍየሎቹ ደግሞ አመት የሞላቸው ሊሆኑ እንድሚገባ በርካታ ዑለማዎች የሚናገሩ ሲሆን የተለየ አቋም ያላቸው ሊቃውንትም አሉ።

የእንስሶቹን ዘካህ የተመለከቱ ጥቅል መመሪያዎች

1) ከአንድ በላይ ባለንብረቶች ያላቸው የዘካህ ከብቶች በአንድ በረት እያደሩ በአንድ የጋራ እረኛ የሚሰማሩ ከሆነ እንደ አንድ ሰው ንብረት ይታሰባሉ። የዘካህ ህጉም ይህንን የተከተለ ይሆናል። አቡ በክር አስ-ሲድ-ዲቅ መልዕክተኛው የደነገጉትን የዘካህ አወጣጥ በዘረዘሩበት ፅሁፋቸው እንዲህ ብለዋል፦

◄ «وَلاَ يُجْمَعُ بَيْنَ مُتَفَرِّقٍ، وَلاَ يُفَرَّقُ بَيْنَ مُجْتَمِعٍ خَشْيَةَ الصَّدَقَةِ»

► «ዘካህ ተፈርቶ የተለያዩ (እንስሶች) አይሰበሰቡም፤ የተሰበሰቡትም አይነጣጠሉም።»

<u>ለምሣሌ</u>፦ ሁለት ግለሰቦች እያንዳንዳቸው 40 በጎች ቢኖሯቸውና ከላይ በተጠቀሰው መልኩ ቢደባልቋቸው ዘካህ የሚያወጡት 1 በግ ብቻ ይሆናል። እያንዳንዳቸው 20 ቢኖራቸውም እንደዚሁ አንድ በግ መስጠት ይኖርባቸዋል። ለዘካህ የምትሰጠው በግ ከአንደኛው ንብረት ትወሰድና ከሌላኛው የዋጋዋን ግማሽ ይቀበላል።

2) ከሶስት ሁኔታዎች በስተቀር ወንድ ከብቶችን ማውጣት አይቻልም፦

❶ አመት የሞላት ሴት ግመል ያጣ ባለሁለት አመት ወንድ መስጠት ይፈቀድለታል።
❷ በሬና ላም ያለው ባለአንድ አመት ወንድ መስጠት ይፈቀድለታል።
❸ ሴት ከብት ጭራሽ የሌለው ከሆነ ወንድ ማውጣቱ ከችግር አንፃር እንደሚፈቀድለት በርካታ ሊቃውንት ይጠቅሳሉ።

3) ለዘካህ የሚሰጡት ከብቶች በጣም ወድ የሆኑት ወይም በጣም የተራከሱት ሳይሆኑ በአንፃራዊ እይታ መካከለኛ የሆኑት ናቸው።

4) የከብቶቹ ቁጥር «ኒሷብ» ከደረሰ በኋላ የሚወለዱ ጥጆችና ግልገሎች ዓመት ባይሞላችውም በዘካህ ሂሳብ ውስጥ ይደመራሉ። ለምሳሌ፦ 120 በጎች በይዞታው ስር ያሉ ግለሰብ በ11ኛው ወር አንዲት ግልገል ብትወለድለት/በት(!) ከአንድ ወር በኋላ ሁለት በጎችን ለዘካህ ያቀርባል።



4- ከምድር የሚወጡ ተፈጥሯዊ ሀብቶች

አላህ በቁርአኑ እንዲህ ይላል፡-

◄﴿يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ أَنفِقُواْ مِن طَيِّبَٰتِ مَا كَسَبۡتُمۡ وَمِمَّآ أَخۡرَجۡنَا لَكُم مِّنَ ٱلۡأَرۡضِ﴾ [البقرة: ٢٦٧]

► *«እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ሰርታችሁ ካገኛችሁት መልካሙን እና ከምድር ካወጣንላችሁ ለግሱ!»* [አል-በቀራ 267]

«ከምድር ካወጣንላችሁ» **የሚለው ገለፃ ሁለት ክፍሎችን ያካትታል፤ እነርሱም፡-**

1ኛ የእርሻ ሰብሎችና ቡቃያዎች

2ኛ ከከርሰ ምድር የሚወጡ ጥሬ ሀብቶች ናቸው።

1ኛ- የእርሻ ሰብሎችና ቡቃያዎች ዘካህ

የእርሻ ባለቤት የሆነ ግለሰብ አዝመራ በተሰበሰበ ጊዜ ከፊሉን ለዘካህ ወጪ ማድረግ ይጠበቅበታል። ይህ የሚሆነው እንደሌሎች የንብረት ዓይነቶች አመትን ጠብቆ ሳይሆን በአዝመራ ወቅት አንድ ጊዜ ብቻ ይሆናል፤ አላህ በቁርአኑ እንዲህ ብሏል፡-

◄﴿وَءَاتُواْ حَقَّهُۥ يَوۡمَ حَصَادِهِۦ﴾ [الأنعام: ١٤١]

► «... በአዝመራውም ቀን ግዴታውን ስጡ» [1]

የአዝርዕትና የጥራጥሬ ዘካህ ግዴታነቱ የሚፀድቀው ከዚህ በፊት ከተጠቀሱት የዘካህ ጥቅል መስፈርቶች ጋር ሌሎች ቅድመ ሁኔታዎች ሲታከሉ ነው።

እነሱም፦

1- አዝርዕቱ በመስፈሪያ የሚለካ ወይም መለካት የሚችል መሆኑ፣

2- በመሠረታዊ ምግብነት (በቀለብነት) የሚያገለግሉና ታጉረው ሊቆዩ የሚችሉ መሆናቸው[2]፤

በእነዚህ ሁለት መሥፈርቶች መሠረት እንደ ስንዴ፣ ገብስ፣ ጤፍ፣ በቆሎ፣ ማሽላ፣ ምስር፣ ተምር፣ ዘቢብ ካሉ እህሎች፣ ጥራጥሬዎችና ፍሬዎች ዘካህ ሊወጣ እንደሚገባ እንረዳለን።
በአንፃሩ ደግሞ እንደ ብርቱካን፣ ሙዝ፣ ማንጎ፣ ፓፓያ፣ ቲማቲም፣ ድንች፣ ካሮት፣ ጎመንና ሽንኮራ ባሉት ቅጠላ ቅጠሎችና ፍራፍሬዎች ላይ ዘካ ግዴታ እንደማይሆን እንገነዘባለን።

3- አዝርዕቶቹና ሰብሎቹ በግለሰቡ ይዞታ ስር ሆነው ለአዝመራ መድረሳቸው፤ ለአዝመራ መድረስ የሚባለው ማሳው የመብሰል

---

(1) ይህ አንቀፅ የዘካህ ዝርዝር ህግጋት ከመደንገጋቸው በፊት በመካ የወረደ ቢሆንም ምርቱ ተጣርቶ ከተሰበሰበ የዘካው ግዴታ እንደሚፀና በማስረጃነት ይቀርባል፤ አንዳንድ የተፍሲር ሊቆች አንቀፁ ዘካህን እንደማይመለከት ቢተነትኑም የሰብል ምርት በይዞታ አመት ማሳለፉ መስፈርት እንዳልሆነ ሁሉም ይስማማል።

(2) ይህንን መስፈርት የማይቀበሉ በርካታ ሊቃውንት አሉ!

ምልክቶች ሲታዩበት ነው። በዚህ መሰረት ለአዝመራ ያልደረሰ ሰብል ከባለቤቱ ይዞታ በምንም ምክንያት ቢወጣ ወይም ቢበላሽ ዘካህ አይመለከተውም፣ አዝመራው ከደረሰ በኋላ (ባይሰበሰብ እንኳ) አዝርዕቱን በስጦታ ወይም በግዢ ለሌላ አካል ቢያስተላልፍ ግዴታው በቀድሞው ባለቤት ላይ ይሆናል! ምርቱ ተጣርቶ ከመሰብሰቡ በፊት ወይም ከተሰበሰበ በኋላ ዘካውን ለማውጣት ሳይችል ከፈቃዱ ውጭ በሆነ ምክንያት ቢወድም ግን የዘካህ ሃላፊነት አይኖርበትም።

ለአዝመራ ከመድረሱ በፊት የተረከበ ባለቤት እንደሆነ ግን አዝመራው ሲደርስ ግዴታው ይመለከተዋል።

4- አዝርዕቱ ከተወቃ በኋላ መጠኑ ቢያንስ 1200 የሁለት ዕጅ ስፍር (مُدّ) መሙላቱ፣ እዚህ ላይ የተጠቀሰው ሸሪዓዊ ገደብ ስፍርን የተመረኮዘ እንጂ ክብደቱን የተመለከተ እንዳልሆነ ማስተዋል ያስፈልጋል። የተከበሩት መልዕክተኛ እንዲህ ይላሉ፡-

◄ «ليس فيما دون خمسة أوسق صدقة»

► *«ከአምስት "አውሱቅ" በታች (ግዴታ የሆነ) ሰደቃ የለም»* [1]

- 1 ወስቅ = 60 “ሷዕ”[2] ፤ 1 ሷዕ = 4 የሁለት እጅ እፍኞች
- 5 አውሱቅ = 5 x 60 ሷዕ = 300 ሷዕ = 300 x 4 እፍኞች = 1200 እፍኞች

---

(1) አል-ቡኻሪ (1447)፤ ሙስሊም (979)፣(980)

(2) በድሮ ጊዜ የነበረ የእህል መስፈሪያ ሲሆን በአገራችን ብዙዎች «ቁና» ብለው ቢተረጉሙትም በመጠን ግን ከቁና ያንሳል።

ይህም ከሞላ ጎደል በደህና የስንዴ ስፍር ሲለካ በትንሹ 612 ኪ.ግ አካባቢ ይመዝናል። ሆኖም የስፍሩ ክብደት እንደየእህሉ አይነት የሚለያይ መሆኑን ማስታወስ ያስፈልጋል።

➔ እህሉ እጅ በእጅ ባይሰፈር እንኳ ከአዝመራው በፊት ልምድ ባላቸው ታማኝ ሰዎች መጠኑ ሊገመት እንደሚችል ብዙሀኑ ሊቃውንት ይስማማሉ። ታዲያ በዚህ መልኩ ሲለካ 1/3ኛውን ወይም 1/4ኛውን ከሂሳቡ ማቃለል እንደሚገባ የሚጠቁም ሐዲሥ ቢኖርም በርካታ የሐዲሥ ሊቃውንት ዘገባው ጠንካራ እንዳልሆነ ያወሳሉ።

- **ለዘካህ ወጪ የሚሆነው መጠን፡-**

አዝርዕቱ ከላይ የተጠቀሰው የስፍር መጠን ያህል ከደረሰ ተሰፍሮ ወጪ የሚሆነው የዘካህ መጠን እንደሚከተለው ይገለፃል፡-

➢ እርሻው በዝናብ፣ በወንዝ ወይም በመስኖና በመሳስሉት ዘዴዎች ውሃ የሚያገኝ ከሆነ ከተሰበሰበው አንድ አስረኛው (10%) ለዘካህ ይሰጣል፤ እነዚህ ላይ የሚታየው ውሃ ለማጠጣት ተደጋጋሚ ልፋት አለመኖሩ ነውና!

➢ ማሳው የገበሬውን ተደጋጋሚ ልፋት በሚጠይቁ የውሃ ማጠጫ ዘዴዎች ውሃ የሚያገኝ እንደሆነ ግን አንድ ሃያኛውን (5%) ብቻ ወጪ ያደርጋል። ይህ ውሃን በተለያዩ ዘዴዎች በመቅዳት፣ ወይም ቋሚ ወጪ በሚያስፈልጋቸው ዘመናዊ የኤሌክትሪክ መሳሪያዎች ወደ እርሻው በማስተላለፍ የሚካሄደውን የማጠጣት ስልት ያካትታል።

የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

◄ "فِيمَا سَقَتِ السَّمَاءُ وَالْعُيُونُ أَوْ كَانَ عَثَرِيًّا الْعُشْرُ، وَمَا سُقِيَ بِالنَّضْحِ نِصْفُ الْعُشْرِ"

►«ሰማይ (ዝናብ) እና ምንጮች ባጠጡት ወይም (ከመሰኖና አቅራቢያው ካለ ውሃ) በስሩ የሚጠጣ እርሻ ላይ አንድ አስረኛ አለበት፤ በሸክም የሚመላለስ ውሃ የሚጠጣ የአንድ አስረኛ ግማሽ አለበት።» (1)

➢ ማሳው ግማሹን አመት በዝናብ (ያለተደጋጋሚ ልፋት) ፣ ሌላውን ግማሽ ደግሞ በማመላለስ (በልፋት) ውሃ የሚያገኝ ከሆነ ወይም በሁለቱም ዘዴዎች እኩል የሚጠጣ ከሆነ ወጪ የሚደረገውም መጠን መካከለኛ እንዲሆን ይሰላል፤ በዚህም መሰረት የአንድ አስረኛ ሶስት አራተኛ (3/40) = (7.5%) ይሆናል።

- <u>የአዝርዕቱን ዘካህ የተመለከቱ ጥቅል መመሪያዎች፡-</u>

➔ የተለያዩ የእህልና የአዝርዕት ዓይነቶች ለየብቻ ሲሰፈሩ በተናጠል «ኒሷብ» ካልደርሱ ዘካህ ማውጣት ግዴታ አይሆንም።

➔ በኪራይ ወይም በተለየ ውል በሌላ ሰው መሬት ላይ እህል የዘራ ግለሰብ የዘካህ ግዴታ ይመለከተዋል፤ የእህሉ ባለቤት እርሱ ነውና። የመሬቱ ባለቤት ከአዝርዕቱ ድርሻ ከሌለው በስተቀር የእህሉ ዘካህ አይመለከተውም።

---

(1) አል-ቡኻሪ (1483)

2ኛ- የጥሬ ሀብት (ማዕድን) ዘካህ

ማዕድን በዚህ አገባቡ የሚወክለው ከከርሰ ምድር በቁፋሮ የሚገኝ ተፈጥሯዊ ጥሬ ሀብትን ሲሆን ዘካህ የሚመለከታቸው የማዕድን አይነቶችን በተመለከተ በሊቃውንት መካከል የሀሳብ ልዩነት ተነስቷል።

ሆኖም "*ከምድር ካወጣንላችሁ ለግሱ*" የሚለው ከላይ ያወሳነው የቁርአን አንቀፅ መልዕክት ጥቅል በመሆኑ በቁፋሮ የተገኘው ማዕድን እንደ ወርቅና ብር በመሰረቱ አመታዊ ዘካህ የሚመለከተውም ይሁን፤ አሊያም እንደ ብረት፣ ነሃስ፣ አልማዝ፣ እምነ በረድ፣ ነዳጅ.. ወዘተ አመታዊ ዘካህ የማይመለከተውም ይሁን፤ ሁሉም ከምድር በሚወጣበት ወቅት የአንድ ጊዜ ወጪ ይደነገግበታል ማለት ነው።

➔ የዘካው ግዴታ የሚጀምርበት እርከን (ኒሷብ) የሚለካው ማዕድናቱ ከተጣሩ በኋላ በሚኖራቸው ዋጋ ሲሆን መጠኑ ደግሞ ከወርቅ ወይም ከብር የኒሷብ ዋጋ አነስተኛው ነው።

ወጪ የሚሆነውም አንድ አርባኛው (2.5%) እንደሆነ ብዙሃኑ የፊቅህ ጠበብት ያሰፍራሉ።

- **ተቀብሮ የተገኘ ቅርስ፡-**

በመሬት ውስጥ ተቀብሮ የተገኘ ድልብ ሀብት ወይም ቅርስ ቀድሞ የሙስሊም ንብረት እንደነበር የሚጠቁም ምልክት ካለው ወይም የሙስሊሞች አገር ላይ ከተገኘ ባለቤቱ ለማይታወቅ የጠፋ ንብረት (لُقَطَة) የሚስሰጠው ኢስላማዊ ብይን ይኖረዋል፤ ይህም ማለት ባለቤቱ ወይም ወራሹ ማን እንደሆነ ለማወቅ ለአመት ያህል ሳያጠያይቁ መጠቀም አይቻልም።

ካልሆነ ግን ጥቅል መጠኑ ይነስም ይብዛም 1/5ኛው (20%) ወጪ ይሆናል። የተቀረው 4/5ኛ እንደሁኔታው ለመሬቱ ባለቤት፣ ባለቤት ከሌለው ደግሞ ላገኘው ግለሰብ ይሆናል።

መልዕተኛው እንዲህ ብለዋል፡-

◄«وَفِي الرِّكَازِ الْخُمْسُ»

► *«በ«ሪካዝ» ላይ አንድ አምስተኛ አለበት (ይሰጣል)።»*[1]

ሆኖም የተገደበ የኒሷብ መጠን የሌለው ከመሆኑ አንፃር፤ እንዲሁም ከወጪ አደራረጉና ከሌሎች ሁኔታዎች አንፃር በዘካህ ህግ ስር የማይካተት ራሱን የቻለ ድንጋጌ መሆኑ የብዙሀኑ ሊቃውንት አቋም ነው።

❀❀❀

(1) **አል-ቡኻሪ** (1499)፣ (2355)፣ (6912)፣ (6913)፤ **ሙስሊም** (1710)

ዘካህ የሚሰጣቸው ወገኖች

የዘካህ ድጎማ የሚገባቸው ወገኖች ስምንት ዓይነት ናቸው። እነርሱም በሚከተለው የአላህ ቃል ተዘርዝረዋል፦

﴿إِنَّمَا ٱلصَّدَقَٰتُ لِلۡفُقَرَآءِ وَٱلۡمَسَٰكِينِ وَٱلۡعَٰمِلِينَ عَلَيۡهَا وَٱلۡمُؤَلَّفَةِ قُلُوبُهُمۡ وَفِي ٱلرِّقَابِ وَٱلۡغَٰرِمِينَ وَفِي سَبِيلِ ٱللَّهِ وَٱبۡنِ ٱلسَّبِيلِ فَرِيضَةٗ مِّنَ ٱللَّهِ وَٱللَّهُ عَلِيمٌ حَكِيمٞ ٦٠﴾ التوبة [٦٠]

▶ «(ግዴታ) ምፅዋትም ለድሆች፣ ለምስኪኖች፣ በሷም ላይ ሰሪዎች ለሆኑ፣ ልቦናቸው (ኢስላምን) የሚላመድ፣ በባሮችም፣ በባለዕዳዎች፣ በአላህምመንገድና፣ (ካገሩለወጣ) መንገደኛ ነች፤ ከአላህ ዘንድ (የተገደበች) ግዴታ፤ አላህም እጅግ አዋቂ፣ ጥበበኛ ነው።»

<u>ማብራሪያው እንዲሚከተለው ይቀርባል፦</u>

1) ድሆች፦ ድሆች የሚባሉት የእለት ጉርሳቸውን በበቂ መልኩ የማያገኙ ናቸው።

2) ምስኪኖች፦ ምስኪኖች የሚባሉት አስፈላጊ የኑሮ ማሟያዎችን የማያገኙ ናቸው።[1]

➔ ድሆችና ምስኪኖች ሊሰጣቸው የሚችለውን ከፍተኛ መጠን አስመልክቶ በሊቃውንት መካከል ውዝግብ ተነስቷል። አመዛኙ አቋም ከድህነት ወጥተው የሚቋቋሙበት ያህል ሊሰጣቸው የሚችል መሆኑ ነው።

---

(1) በድሃ (الفقير) እና በምስኪን (المسكين) መካከል ያለውን የትርጉም ልዩነት አስመልክቶ በርካታ ሀሳቦች ተሰንዝረዋል።

ነብያችን ንብረቱን በአደጋ ያጣ ወይም ድህነት ያጋጠመው ሰው እርዳታ መጠየቅ የሚችልበትን ገደብ ሲያወሱ *"የኑሮ ግዴታውን የሚደግፍበት (የሚሸፍንበት) መጠን እስኪያገኝ"* [1] ማለታቸው ይህንን ያሳያል።

ሆኖም የዘካህ ድጎማ ይበልጥ የሚያስፈልጋቸውን ወይም አንገብጋቢ ሁኔታ ላይ የሆኑትን ችግረኞች ድርሻ በሚያስቀር መልኩ መሆን የለበትም።

➔ የሚታከምበት የሌለው ድሃ ለህክምናውና ለተያያዥ ወጪ ከዘካህ ሊደጎም ይችላል።

3) **የዘካህ ሰብሳቢዎችና አከፋፋዮች፡-** እነርሱም የሙስሊሞች የበላይ መሪ ዘካህን እንዲሰበስቡና እንዲያከፋፍሉ የመደባቸው ወይም የፈቀደላቸው ሲሆኑ ለዚህ ስራቸው ከዘካህ ገንዘብ እንደልፋታቸው አበል ይቆረጥላቸዋል።

4) **ልቦናቸው (ኢስላምን) የሚላመድ፡-** እነኚህም ኢስላምን ለመቀበል ዝንባሌ ያላቸው፣ ወይም አዲስ ሰለምቴዎች ሆነው እምነታቸው ያልጠነከረ ግለሰቦች ሲሆኑ የዘካህ መልካም አድራጎት ለእምነታቸው መስተካከልና መሻሻል አስተዋፅኦ እንደሚያበረክት ከተገመተ ከዘካህ ወጪ ውስን ድርሻ ይኖራቸዋል። ሙስሊሞች ላይ የተንጣበበ አደጋን ለማስቀረት ተሰሚነት ላላቸው ግለሰቦች መክፈል ብቸኛው አማራጭ ከሆነም ከዘካህ ወጪ ሊደረግ ይችላል።

5) **በባርነት ሥር ያሉ ሙስሊም ወገኖች፡-** በባርነት የሚገዙ ሙስሊሞችን ገዝቶ ነፃ ለማውጣት ወይም በተወሰነ ክፍያ ነፃነታቸውን

---

(1) ሙስሊም (1044)

ለማግኘት ከአሳዳሪዎቻቸው ጋር ውል የፈፀሙትን በክፍያ ለማገዝ ከዘካህ ገንዘብ ወጪ ይደረጋል።

➔ አንዳንድ ሊቃውንት ሙስሊም ምርኮኛን ለማስለቀቅ የሚከፈል ቤዛ በዚሁ ፍርድ ውስጥ እንደሚካተት ይናገራሉ።

6) **የእዳ ጫና ያለባቸው፡-** እዳቸውን መክፈል የሚችሉበት መጠን ከዘካህ ይሰጣቸዋል።

ባለዕዳዎች ሁለት ዓይነት ናቸው፡-

❶ ለራሳቸው ጥቅም (ለወጪያቸው) ወይም በግል ስህተታቸው ምክንያት እዳ የተጫነባቸው፤

- እነዚህ እዳውን መክፈል የተሳናቸው ካልሆኑ በቀር ዘካህ ሊሰጣቸው አይገባም፤ ስለሆነም ተሽሮ እዳቸው ሊከፈልበት የሚችል (ለኑሮ ግዴታ የማያስፈልግ) ትርፍ ንብረት ካላቸው ዘካህ አይገባቸውም።
- ዘካው እንደአስካሪ መጠጥ ላሉ ለተከለከሉ አገልግሎቶች የእዳ ክፍያ የሚውል ከሆነ አይሰጣቸውም። ሆኖም ከሌላ ተበድረው ለሐራም በማዋላቸው ወይም በተከለከሉ አገልግሎቶች ላይ ወጪ በማባከናቸው የተነሳ የገቡበት እዳ ቢሆን ለጥፋታቸው ተውበት (ንሰሃ) ማድረጋቸው ከተንፀባረቀ ብቻ ይደጎማሉ።

❷ በሙስሊሞች መካከል የሚከሰት አስጊ ጠብን ለማብረድ የካሳ ዋስትና የተሸከሙ፤

- እነዚህ የግል ሀብት ቢኖራቸውም ለዘካህ ድጎማ ተገቢ ናቸው።

➔ ሌላ ሰው ዘንድ በእዳ መልክ ገንዘብ ያለው ግለሰብ ዘካህን በመስጠት እሳቤ ገንዘብ ሳያወጣ ከባለዕዳው እዳን ማቃለሉ ወይም መሰረዙ የራስን ጥቅም ማስጠበቅ ነውና እንደዘካህ አይቆጠርም።

➔ ክፍያ ያላስቀረ ሚችን እዳ ከዘካህ መክፈል የሚሰጠውን ብይን አስመልክቶ በዑለማዎች መካከል ሁለት አቋሞች የተንፀባረቁ ሲሆን አብዛኛዎቹ ይህ እንደማይቻል ይስማማሉ።

7) በአላህ መንገድ ላይ ታጋይ የሆኑ፡- ከሙስሊሞች ግምጃ ቤት ተቆራጭ የሌላቸው ታጋዮች የግል ሀብት ቢኖራቸው እንኳ ለ«ጂሃድ» የሚያስፈልጋቸው ወጪ ከዘካህ ይመደብላቸዋል። ለትግሉ የሚስፈልጉ መሳሪያዎችና መሰል ወጪዎችም በዘካህ ሊሸፈኑ ይችላሉ።

➔ ብዙሀኑ ሊቃውንት ይህ መልዕክት የተጠቆመበት ቁርዓናዊ ቃል (وَفِي سَبِيلِ ٱللَّهِ) ሌሎች ጥቅል ሰናይ አድራጎቶችን እንደማያካትት አስረግጠው ይናገራሉ። በዚህም መሠረት መስጂድ ለመገንባት፣ ት/ቤቶችን ለማቋቋም፣ የሕክምና ማዕከላትን ለመመሥረትና ለመሳሰሉት የበጎ ተግባር መስኮች የዘካህ ገንዘብን ማዋል የማይፈቀድ ይሆናል ማለት ነው።

ሆኖም አንዳንድ ሊቃውንት ወደ ኢስላም የሚጣሩና የጠላቶችን ውሸጉብር የሚገልጡ አዋቂዎች በአላህ መንገድ ላይ በእውቀታቸው የሚታገሉ በመሆናቸውና ይህም አንዱ የጂሃድ መስመር በመሆኑ ለዚህ ተግባራቸው አጋዥ እንዲሆን የዘካህ ድጎማ እንደሚገባቸው ይገልፃሉ። ለተመሳሳይ አላማ ጠቃሚ መፅሐፍትን አትሞ ማሰራጨትም በዚህ ስር እንደሚካተት የሚያወሱ አሉ።

8) ወደ አገሩ የሚመለስበት ወጪ ያጣ መንገደኛ፡- እንዲህ ዓይነቱ በመኖሪያ አገሩ በቂ ሀብት ቢኖረው እንኳ ወደ አገሩ መመለሻ የጉዞ ወጪ ከዘካህ ገንዘብ ይሰጠዋል።

❀❀❀

የዘካህ አሰጣጥን የተመለከቱ ጥቅል ነጥቦች

- ከአዝርዕትና ማዕድን በስተቀር ያሉ የዘካ ንብረቶች ከ«ኒሷብ» እስካልጎደሉ ድርስ አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በየአመቱ የዘካህ ወጪ ይመለከታቸዋል።

- **ዘካህን ለዘመድ መስጠት፡-** ማስተዳደሩ ግዴታ ላልሆነ ዘመድ ዘካህን መስጠት ይፈቀዳል። ወጪያቸውን መሸፈን ግድ ለሚል የቅርብ ዘመዶች መስጠቱ ግን ወጪን በማስቀረት እራስን መጥቀም በመሆኑ የተከለከለ ይሆናል። በዚህም መሠረት ለወላጆችና ለወላጆቻቸው፣ ለልጆችና ለልጆቻቸው፣ ለሚስቶች ዘካህ መስጠት ይከለከላል። ሆኖም ያለባቸውን እዳ መክፈል መሰረታዊ ግዴታ ስላልሆነ ለእዳው ክፍያ ከዘካህ ቢሰጣቸው እንደማይከለከል ያወሱ ጥቂት ዑለማዎች አሉ። ግለሰቡ የወጪ ግዴታውን ስላዘገየባቸው የገቡበት እዳ ከሆነ ግን ቀድሞውኑ ሊከፍለው የሚገባው ግዴታ በመሆኑ በዘካህ ሊሸፍነው አይችልም።

- **የአላህ መልዕክተኛ ቤተሰቦችና ዝርያዎች (በኑ ሃሺም)፡-** የዘካ ድጎማን መቀበል አይችሉም፤ ከባርነት ነፃ ያወጡት ግለሰብም እንዲሁ።

- ከላይ በ4 ቁጥር ከተጠቀሱት (ኢስላምን ከሚላመዱት) በቀር ሙስሊም ላልሆነ ሰው ዘካህ መስጠት አይቻልም። ከዘካህ ውጪ ያለ ተራ ምፅዋት መሰጠት ግን አይከለከልም ።

- በቂ ሀብት ባይኖረውም ሰርቶ ለማግኘት <u>አቅሙና እድሉ</u> ያለው ድሃ የዘካህ ገንዘብ አይሰጠውም።

◄ عَنْ عُبَيْدِ اللهِ بْنِ عَدِيِّ بْنِ الْخِيَارِ: أَخْبَرَنِي رَجُلَانِ: «أَنَّهُمَا أَتَيَا النَّبِيَّ – صلى الله عليه وسلم – فِي حَجَّةِ الْوَدَاعِ، وَهُوَ يَقْسِمُ الصَّدَقَةَ، فَسَأَلَاهُ مِنْهَا، فَرَفَعَ فِينَا الْبَصَرَ، وَخَفَضَهُ، فَرَآنَا جَلْدَيْنِ فَقَالَ: "إِنْ شِئْتُمَا أَعْطَيْتُكُمَا، وَلَا حَظَّ فِيهَا لِغَنِيٍّ، وَلَا لِقَوِيٍّ مُكْتَسِبٍ".»

► ***ዑበይዱሏህ ኢብኑ ዐዲይ ኢብኒ'ል-ኺያር እንዲህ ይላሉ፦ ሁለት ሰዎች እንደነገሩኝ መልእክተኛው በመሰናበቻው ሐጅ ላይ ምፅዋት እያከፋፈሉ ወደ እርሳቸው መጡና ከምፅዋቱ እንዲሰጡዋቸው ጠየቋቸው። "እርሳቸውም እይታቸውን ከፍ እና ዝቅ አድርገው ሲመለከቱን ብርቱ መሆናችንን አዩ" (አሉ)፤ ከዚህያም እንዲህ አሉ፦ "ከፈለጋችሁ እሰጣችኋለሁ፤ ለሃብታምና መሰራት ለሚችል ብርቱ ከምፅዋት ድርሻ የላቸውም።"*** (1)

ሆኖም ግለሰቡ ከስራ የታቀበው የሸሪዓ እውቅትን በመማር እንደተጠመዱ ተማሪዎች ወይም አስተማሪዎች ኢስላምን በሚጠቅም አላማ ጊዜውን ስለሚያሳልፍ ከሆነ ሊሰጠው ይችላል።

- የዘካህ ድጎማ የሚገባው ሰው የተቀበለውን ወይም ከፊሉን ለሀብታም ወይም ለሌላ በስጦታ ወይም በሌላ መልኩ ማስተላለፉ አይከለከልም።

- የተሟላ ኒሷብ ያለው ባለ ሀብት ከጊዜው በፊት ዘካውን አስቀድሞ ማውጣት ይችላል። በዘካህ የሚሸፈን አጣዳፊ ችግር ሲኖር ይህ የተወደደ ይሆናል። ወደፊት የንብረቱ መጠን ላይ ጭማሪ ከተከሰተ የወጪውን ልዩነት አስልቶ መክፈል ያስፈልጋል።

---

(1) አሕመድ (17972፣ 23063)፣ አቡ ዳዉድ (1633)፣ አን-ነሳኢይ (2598)

- ዘካህ በሚሰጥበት ጊዜ ዘካህን አቅዶ ያልሰጡት ወጪ ተቀባይነት የለውም። ሆኖም ሲሰጡ ዘካህ እንደሆነ ለተቀባዩ መንገር ግዴታ አይደለም።

- አስፈልጊውን ጥንቃቄ ከማድረጉ ጋር በስህተት ዘካውን ለማይገባው ሰው ከሰጠ በኋላ ያወቀ ዳግም የማውጣት ግዴታ እንደሌለበት በርካታ ሊቃውንት ይፈርዳሉ። ጥርጣሬ ኖሮት ወይም ማጣራት እየቻለ ሳያጣራ የሰጠ ከሆነና የማይገባው ሰው እጅ መግባቱ ከታወቀ ግን ደግሞ ማውጣት ይኖርበታል።

- ዘካህ ግዴታ የሆነበት ሰው ወቅቱ ከደረሰ በኋላ ያለ በቂ ምክንያት ማዘግየት የለበትም። በረመዳን ለማውጣት ማቀድ ጊዜው የደረሰውን ዘካህ ለማቆየት የሚያስችል ተቀባይነት ያለው ምክንያት አይደለም።

- የዘካህ ግዴታነት መስፈርቶች ከተሟሉ በኋላ ያልተሰጠ ወጪ ለአመታት ቢቆይ እንኳ እንደ እዳ ታስቦ መከፈሉ የግድ ነው። ባለቤቱ ቢሞትም ንብረቱ ከመከፋፈሉ በፊት የዘካው ድርሻ ሊወጣ ይገባል። ሆኖም ዘካውን ማውጣት ከመቻሉ በፊት ተጠያቂ በማይሆንበት (ውጫዊ) ምክንያት ንብረቱ ቢጠፋ ወይም ቢወድም የመክፈል ግዴታ አይኖርበትም፤ ማውጣት እየቻለ አዘግይቶት ከሆነ ግን እዳ ይሆንበታል።

- የዘካውን ወጪ በስራ አልምቶና አብዝቶ ለድሆች በመደጎም እሳቤ በንግድና መሰል ፕሮጀክቶች ላይ ማዋል አይፈቀድም። ይህን ለማድረግ ዘካው ሊሰጠው የነበረው ውስን ተቀባይ ፈቃድና ውክልና ያስፈልጋል።

- የሚሰጠውን በአግባቡ ለማይጠቀም፣ ለሚያባክን ወይም በተከለከለ ነገር ላይ ለሚያውል ተረጂ በዘካው ገንዘብ የሚያስፈልገውን ቁሳቁስ ገዝቶ መስጠት ይቻላል።

- ዘካህን ከአንድ አገር ወደ ሌላ አገር ማሻገር፡- አመዛኝ ጥቅም የሚያስገኝ ከሆነ እንዲሚፈቀድ በርካታ ሊቃውንት ይጠቅሳሉ። ማሻገሩ አመዛኝ ጥቅም ከሌለው ግን ንብረቱ ባለበት አገር ያሉት ድሆች ቅድሚያ ሊሰጣቸው እንደሚገባ የሊቃውንት ስምምነት ተጠቅሷል።

❀❀❀

አላህ ይበልጥ አዋቂ ነው።